# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 057 ጥቅምት 27 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ኢትዮጵያ ረሃብን በመዋጋት ተሞክሮ የሚሆን ውጤት አስመዝግባለች



በሞገስ ፀጋዬ እና በአዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት ረሃብን በመዋጋት ረገድ ተሞክሮ የሚወሰድበት ውጤት ማስመዝገቧን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንትና መካሄድ በጀመረው «ከረሃብ ነፃ ዓለም መፍጠር» በተሰኘው ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በድህነት ቅነሳና የምግብ ሉዓላዊነት ማረጋገጥ ሥራዋ የላቁ ተግባራትን እየፈጸመች ትገኛለች፡፡

በተለይ በስንዴ ልማት ሥራዎች ለሌሎች ተሞክሮ ሊሰጡ የሚችሉ የግብርና ሥራዎችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ እየከወነች መሆኑን ተናግረዋል።

የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረትና የግብርና ግብዓት አቅርቦት እጥረት ፈተና መሆኑን ጠቁመው፤ ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በግብርና ማሻሻያ ላይ ትኩረት ሰጥታ መሥራቷንና ድርቅን መቋቋም የሚችሉ ሰብሎችን በመዝራት ምርታማነት ማሳደጓን ጠቁመዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ዓለምን የተፈታተኑ ታላላቅ ችግሮች ቢኖሩም ጥረትን በእጥፍ በመጨመርና ፈጠራ የታከለባቸውን ሥራዎች በመተግበር ፈተናዎችን መቋቋም ተችሏል። ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት በግብርና ምርታማነት ላይ ስትራቴጂካዊ ለውጥ በማምጣት ሰፋፊ ድሎችን ማስመዝገብ ችላለች።

በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጨመረ ከመጣው የሕዝብ ቁጥር አንጻር የምግብ ፍላጎት በእጅጉን ማደጉን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህን ፍላጎት ለመመለስም

ኢትዮጵያ ረሃብን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል











## ከረሃብ ነፃ ዓለምን በመፍጠር የኢትዮጵያ ሚና

ገጽ 8

# አሳሳቢው የሱስ ተጠቂነት እና መዘዙ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

የዓለም መድኃኒት ድርጅት እ.ኤ.አ በ2019 ያወጣው መረጃ እንደሚያመላክተው ከሰባት ሰዎች መካከል አንዱ የሱስ ተጠቂ ነው፡፡ በኢትዮጵያን በተማሪዎች ላይ የሚስተዋለውን ሱስ አስያዥ ዕፅ አጠቃቀምን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ2021 በተጠናው ጥናት በአፍላ እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ወጣቶች ዘንድ የሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮች ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡

በጥናቱ እንደተገለጸው፤ ሱሰኝነት በይበልጥ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ዘንድ ተስፋፍቷል፡፡ ወጣቶቹ በተለይ አዕምሮን ለማንቃት ብለው የሚጠቀሟቸው ንጥረ ነገሮች (Psychoactive Substances) ለከፍተኛ የጤና ችግር አልፎም ሞትን ለሚያስከትሉ በሽታዎች እያጋለጣቸው እንደሚገኝም በጥናቱ ተቀምጧል፡፡

አሳሳቢው የሱስ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ አቪዬሽን ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው

ሄለን ወንድምነው



ፎቶ፡- ገበሀ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ አቪዬሽን ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ ተናገሩ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ "ኢትዮጵያ የምድረ ቀደምት መገኛ" የሚል ስያሜ የተሰጠውን ግዙፉ የመንገደኞች አውሮፕላን ኤ350-1000 ትናንትና በአዲስ አበባ ተረክቧል። አውሮፕላኑ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርስ በተደረገ መርሐ-ግብር ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ እንደተናገሩት፤ የአየር መንገዱን የመሪነት ሚና የሚያስቀጥል እና ሀገሪቱን የዓለም አቀፍ አቪዬሽን ማዕከል የሚያደርጉ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

ግዙፉ ኤ350-1000 አውሮፕላን ወደኢትዮጵያ መግባቱ የአየር መንገዱን ስም ይበልጥ ከፍ የሚያደርግ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ ባለፈ፤ ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሀብት መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ማዕከል ለማድረግ እንዲሁም ከሀገራት ጋር ያለውን የኢኮኖሚ እና የንግድ ትስስር ለማጠናከር በርካታ ሥራዎች ታቅደው እየተሠሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዓመት ከ100 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን

ኢትዮጵያን የዓለም ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል




# የልማት ድርጅቶችን ዕዳ ለመክፈልና የንግድ ባንክን ካፒታል የሚያሳድግ ቦንድ ሊሸጥ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተበድረው ያልመለሱትን ዕዳ ለመክፈል እና የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ የሚውል የመንግሥት የቦንድ ሽያጭ እንዲወጣ የሚፈቅድ ረቂቅ አዋጅ በአብላጫ ድምፅ አፀደቀ፡፡

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንትና አራተኛ መደበኛ ስብሰባውን ሲያካሂድ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ጫና የሚቀንስና ካፒታሉን ከፍ የሚያደርግ ረቂቅ አዋጅ አፅድቋል።



ስለረቂቅ አዋጁ ማብራሪያ ያቀረቡት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር)፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰዱትን ብድር ለመክፈል ባለመቻላቸው በመንግሥት ዕዳ ሰነድ ወይንም ቦንድ እንዲከፈል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀገሪቱ የንግድ ባንክ እንቅስቃሴ ውስጥ የያዘውን ከፍተኛ ድርሻ ይዞ እንዲቀጥል ለማድረግ ደረጃ በደረጃ ካፒታሉን ማሳደግ ማስፈለጉን አመልክተዋል፡፡

የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰዱትን ብድር በወቅቱ ባለመመለሳቸውና የብድር ወለዱም በጣም ከፍ በማለቱ በባንኩ ላይ ከፍተኛ ጫና ማስከተሉንም አንስተዋል፡፡ ባንኩ የሀገሪቱ ዋነኛ የፋይናንስ ተቋም በመሆኑ በብድር የተወሰደው 900 ቢሊዮን ብር የመንግሥት ዕዳ ሰነድ ሆኖ እንዲከፈል መወሰኑን አስታውሰዋል።

በታቀደው መሠረት ዕዳውን ለመክፈል የሚያስችል በቂ የገንዘብ ምንጭ ሊገኝ ባለመቻሉና ዕዳው ሳይከፈል በመቆየቱ የወለድ ሂሳቡ የዕዳውን ጫና እያከበደው በመሄድ ላይ እንደሚገኝ በመጠቆም ርምጃ መውሰድ ማስፈለጉን ተጠሪ ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከብር 845 ቢሊዮን 316 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተሰበሰበ ሂሳብ ይዞ መቆየቱ በባንኩ የፋይናንስ ገጽታ ላይ አሉታዊ ውጤትን በማስከተሉ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በፈጠሩት ችግር ተግዳሮት ውስጥ ያለውን ባንክ ለመታደግ ምክር ቤቱ ኃላፊነት ሊወስድ እንደሚገባው፣ የቦንድ ሽያጩን አካሂዶ ወደ ጤናማ አቋም መመለስ ተገቢ በመሆኑ አዋጁን እንደሚደግፉት ተናግረዋል፡፡

የልማት ድርጅቶቹ የሕዝብን ጥያቄ በብቃት የማይመልሱ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ያለባቸው፣ ሀገርን ለከፍተኛ ዕዳ የዳረጉ በመሆናቸው የአስተዳደር ችግር ሁኔታቸው ጭምር ታይቶ በተጠና መንገድ ውሳኔ ሊያገኙ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ለዚህም ተቋማቱን የሚከታተላቸው ቋሚ ኮሚቴ የልማት ድርጅቶቹ ያሉበትን ሁኔታና ከገቡበት ችግር የሚወጡበት መንገድ በዝርዝር አጥንቶ እንዲያቀርብ ጠይቀዋል፡፡

የስኳር እና የማዳበሪያ ፋብሪካዎች በሚል እንደትልቅ እመርታ ሲጠቀሱ የነበሩ ተቋማት ሃገራዊ ውድቀት ማስከተላቸው አንድምታው ሊብራራ እንደሚገባ አንስተው፤ ከለውጡ በፊትም ሆነ በኋላ በሀገር ሀብት ብክነት ዙሪያ ተጠያቂነት ሊሰፍን ይገባል ሲሉም ጠይቀዋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)፤ የልማት ድርጅቶቹ ከፍተኛ የአሠራር ችግር የነበረባቸውና ሳይጠኑ ወደሥራ የገቡ እንደነበሩ አስታውሰዋል፡፡ ተቋማቱን ለማስተካከልና ዕዳውን ወደ ምንዳ ለመቀየር ባለፉት ስድስት ዓመታት በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውንም ገልጸዋል፡፡

በትግበራው በርካታ ተቋማት ከነበሩበት አዘቅት ወጥተው ወደትርፋማነት መሸጋገራቸውን ጠቁመው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድና ኢትዮ ቴሌኮም በአሕጉር ደረጃ ጭምር ተወዳዳሪ መሆን መቻላቸውን አንስተዋል፡፡

አሁን የተነሳው ያደረና የከረመ ችግር ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተወስዶ ሳይከፈል የቀረ ዕዳ በዚህ ደረጃ ከፍ ያለው በየጊዜው ሊከፈል ባለመቻሉና ወለዱ እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ጉዳዩን ከመሠረቱ ለመፍታት በመጀመሪያ ዙር የዕዳ እና ሃብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን በማቋቋም ዕዳውን እንዲተላለፍ በማድረግ በርካታ ተቋማት ዕዳቸው ተሻሽሎ ጊዜያዊ መፍትሔ ማግኘታቸውንም ተናግረዋል፡፡

ዘላቂ መፍትሔ እንዲገኝ ለማድረግ ጉዳዩን ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር በመውሰድ በብድር ሰነድ መክፈሉ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን የገለጹት እዮብ (ዶ/ር) እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በጭራሽ እንዳይደገም የልማት ድርጅቶቹ የሚመሩበት ሁኔታ በመሠረታዊነት መቀየሩንም አመልክተዋል፡፡

በተጨማሪ ምክር ቤቱ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን ማሻሻያንና ኢትዮጵያ ከማልታና ከቻድ ሪፐብሊክ መንግሥታት ጋር ያደረገቻቸውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ አዋጆች አፅድቋል።



ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ

# ባለሥልጣኑ ከ30 ተቋማት ጋር የፈጠረው ቅንጅት ውጤታማ መሆኑን ገለጸ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከ30 ተቋማት ጋር እያከናወነ የሚገኘው ቅንጅታዊ ሥራ ውጤት እንዳስገኘለት የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ገለጸ። የኮሪደር ልማት እና መሠረተ ልማቶች መጠበቅ የሚያስችል አሠራር መዘርጋቱን አስታውቋል።

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ባለሥልጣኑ ከ30 ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራቱ ውጤታማ ሆኗል።

ተቋማቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ትስስር መፍጠሩን ጠቁመው፤ ከአዲስ አበባ ፖሊስ፣ ከሴቶች እና ሕፃናት ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከፍትሕ ቢሮ፣ ከንግድ ቢሮ፣ ከትምህርት ቢሮ እና ሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

ፅዳትን እንዲሁም የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የኮሪደር ልማቱ ንፅሕናው እንዲጠበቅ የቁጥጥር ሥራ መከናወኑን አንስተው፤ በልመና የሚተዳደሩ ሰዎችን እንዲሁም ጎዳና ላይ የሚገኙ አቅመ ደካሞች በማንሳት ወደማዕከላት የማስገባት ሥራ መከናወኑን ጠቁመዋል።

በተያዘው በጀት ሩብ ዓመት ከሴቶች እና ሕፃናት ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በመሆን ከሰባት ሺህ በላይ የጎዳና ተዳዳሪዎችን እንዲሁም በልመና ሥራ የሚተዳደሩት በማንሳት ወደ ማዕከላት እንዲገቡ መደረጉን አስታውቀዋል። በተጨማሪ ከአንድ ሺህ 500 በላይ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የግንዛቤ መስጫ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ መደረጉን ጠቁመዋል።

ከፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር ከመደበኛ ሥራዎች ባሻገር ቅንጅታዊ አሠራር በመተግበር በከተማዋ ፅዳት ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር የአቅም ግንባታ ሥራዎች ከወረዳ እስከ ማዕከል መሠራቱን አንስተዋል፡፡

ከተማዋ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የምታስተናግድ ከመሆንዋ ጋር ተያይዞ በተለይ ከአዲስ አበባ ፖሊስ፣ ከሠላም ሠራዊትና ከተለያዩ የፀጥታ አካላት ጋር በመሆን በተሠሩ ሥራዎች የፀጥታ ሁኔታ በማስጠበቅ ረገድ ውጤታማ ክንውን ታይቷል ብለዋል።

በሕግ የተያዙና በከተማ አስተዳደሩ የሚፈለጉ እንዲሁም ለተለያዩ ሥራዎች የሚውል መሬትን ላልተገባ ዓላማ እንዳይውል የመጠበቅ ሥራ እንደሚከናወን ጠቁመዋል። በሚሊዮን ካሬ የሚለካ መሬትን በመጠበቅ ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ 27 ቦታዎችን ለከተማው አስተዳደር በማስረከብ ለልማት እንዲውሉ መደረጉን አስታውቀዋል።

ከንግድ ቢሮ ጋር በተሠሩ የቁጥጥር ሥራዎች የንግድ ሥርዓቱን ከማስጠበቅ አንፃር ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ ምርት የሚደብቁ ነጋዴዎች ላይ ርምጃ መወሰዱን አንስተዋል። ባለፉት ሦስት ወራት በሕገወጥ መንገድ የተገኘ ከ200 ኩንታል በላይ በርበሬ እና ከስምንት ሺህ ሊትር በላይ ዘይት መያዙን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሕገወጥ ንግድን በመከላከል ሥራ የከተማዋ አደባባዮች ሙሉ በሙሉ ከሕገ ወጥ ንግድ ነፃ እንዲሆኑ መደረጉን ጠቁመዋል።

የተለያዩ የደንብ ጥሰት ፈጽመው በተቀመጡላቸው የቅጣት አይነቶች ላይ በጊዜው ክፍያ የማይፈጽሙ ግለሰቦችና ተቋማት ላይ ከፍትሕ ቢሮ ጋር በመተባበር ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።



አባገዳ ጃርሶ ዱጎ



ራሃ ሙዘሚል



አቶ ሞዳ ቦረናገዲ

# “ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርገውን መንገድ በመምረጥ ችግሮችን በምክክር መፍታት ይገባል”

## - የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርገውን ሠላማዊ መንገድ በመምረጥ ችግሮችን በምክክር መፍታት ይገባል ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች ገለጹ፡፡

ኢፕድ ያነጋገራቸው የጉጂ አባገዳ የሆኑት አባገዳ ጃርሶ ዱጎ እንደተናገሩት፤ ልዩነቶችን በሠላማዊ አካሄድ በምክክር መፍታት ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ ተግባር ነው።

በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ልዩነቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት ይኖርበታል ያሉት አባገዳ ጃርሶ፤ ከመገፋፋት ይልቅ ችግሮችን በምክክር በመፍታት ሠላምን ማስፈን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የጉጂ፣ ሜጫ፣ ቱለማ፣ ሲኮ መንዶ፣ አባገዳዎችም መክረው በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው ጠቅሰው፤ በምክክሩ ላይም መግባባትንና መቀራረብን ማምጣት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ለመምከር መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡

ሠላም የሁሉም ነገር መሠረት በመሆኑ ችግሮችን በምክክር መፍታት ያስፈልጋል የምትለው ደግሞ ከጅማ ዞን ሊሙሰቃ ወረዳ የመጣችው ወጣት ራሃ ሙዘሚል ናት፡፡

ሁሉም ሰው ምክክር በማድረግ ወደ ሠላም መምጣት አለበት ያለችው ወጣት ራሃ፤ ምክክርን አማራጭ ማድረግ ልዩነቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት እንደሚያስፈልግም ጠቁማለች፡፡

ልዩነቶችን በግጭት ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ በመምከር መፍታት ተገቢ ነው የሚሉት ደግሞ የጫንጮ ከተማ ነዋሪው አቶ ሞዳ ቦረናገዲ ናቸው፡፡

ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅመው ከግጭት ይልቅ በሠላማዊ መንገድ ምክክር በማድረግ ልዩነቶችን መፍታት ነው ያሉት አቶ ሞዳ፤ መግባባት፣ መመካከር፣ ወደ ሠላም መምጣት እና ችግሮችን በውይይት መፍታት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ማንኛውም ሰው ያለውን ጥያቄ ማቅረብ ያለበት በሠላማዊ መንገድ መሆን እንዳለበት ጠቅሰው፤ ልዩነቶችንና ጥያቄዎችን ሀገራዊ ምክክርን በመጠቀም ወደ መፍትሔ፣ ሠላም፣ አንድነትና ልማት መምጣት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክር ችግሮቻችንን ለመፍታት ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ሁሉም ሰው ይሄን ዕድል መጠቀም አለበት ያሉት አቶ ሞዳ፤ የትኛውም ሰው ያለውን አጀንዳ በሠላማዊ መንገድ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ማቅረብ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

የተለያዩ ሀገራት ምክክር አካሂደው ሀገራዊ መፍትሔ በማምጣት ችግሮቻቸውን መፍታት መቻላቸውን ጠቅሰው፤ ምክክሩ ለሀገር ትልቅ መፍትሔ ይዞ መምጣት የሚችል በመሆኑ በንቃት እንደሚሳተፉ አንስተዋል፡፡

የአዳማ ከተማ ነዋሪዋ ወይዘሮ ሄለን ከበደ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ ሠላማዊ ሁኔታን ለመፍጠር፣ መግባባትንና ፍቅርን ለማጠናከር ምክክር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ምክክር የኢትዮጵያ ሕዝብ ተግባብቶ በሠላም አብሮ እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል የሚሉት ወይዘሮ ሄለን፤ ወጣቶች የሠላም ተምሳሌት በመሆን በሀገሪቱ ሠላምና አንድነት እንዲሰፍን የድርሻውን ሊወጡ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ወጣቶች በሀገራዊ ምክክሩ ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ልዩነቶችን በሠላማዊ መንገድ ሊፈቱ እንደሚገባቸውም መልዕክት አስተላልፈዋል።

# “አሕጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነቱ አጀንዳ 2063ን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል”

\- *ያስሚን ወሃረቢ*
*የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ*

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት አጀንዳ 2063ን ተግባራዊ የሚያደርግ ነው ሲሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ያስሚን ወሃረቢ ገለጹ።

የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሴክሬቴሪያት ከፍተኛ የንግድ ባለሙያዎች ጉባኤ ከትናንት ጀምሮ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር የንግድ ትስስርና የወጪ ንግድ ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ያስሚን ወሃረቢ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ጉባኤው አጀንዳ 2063 ተግራዊ የሚደረግበት ነው።

ጉባኤው በአሕጉሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የጋራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የንግድ ትስስር የሚፈጠርበት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከጥቅምት 11 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ መቆየቱን ጠቁመዋል። በቀጣይም ከጥቅምት 30 እስከ ኅዳር 1 ቀን 2017 ዓ.ም የንግድ ሚኒስትሮች የጋራ ጉባኤ እንደሚደረግ አመላክተዋል። ስብሰባው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚካሄድ መሆኑንም አስረድተዋል።

የአፍሪካ አጀንዳ 2063 አሕጉራዊ ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ እንዲሁም ማኅበራዊ እድገት ለማረጋገጥ ከታቀዱ ፕሮጀክቶች መካከል የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነት አንዱ ነው ብለዋል።

ዋና ዓላማውም በፓን አፍሪካን ራዕይ አሕጉራዊ የኢኮኖሚ ውሕደት በማስፋት የዕቃዎችና አገልግሎት ገበያን መፍጠር፣ የአፍሪካን ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የካፒታልና የሰዎችን ነፃ እንቅስቃሴ በማመቻቸት ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ፕሮጀክቱ በጥቅሉ ሦስት ነጥብ አራት ትሪሊዮን ዶላር ያላቸው ሀገራትን እና ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን በላይ የሆነውን ሕዝብ ጥቅል አሕጉራዊ የልማት ምጣኔን የሚያሳድግ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

ጉባዔው በሀገራችን መካሄዱ ኢትዮጵያ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታ ጀምሮ ለአፍሪካዊ ጉዳዮች ያላትን አጋርነት እንዲሁም ስምምነቱን እንደ ሀገር ለመተግበር ያላትን ቁርጠኝነት ማሳያ ነው ብለዋል። በተጨማሪም የንግዱ ማኅበረሰብና መላው ኅብረተሰብ በጉዳዩ ላይ ያለው ግንዛቤ ለመጨመር እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

ጉባኤው ለተከታታይ ሦስት ቀናት የሚቆይ ሲሆን አንድ የአፍሪካ ገበያን የመፍጠር እሳቤ ያነገበ ስለመሆኑም ተጠቁሟል።

የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት እ.ኤ.አ መጋቢት 21 ቀን 2018 በሩዋንዳ ኪጋሊ በተካሄደ የአፍሪካ ሀገራት የመሪዎች ጉባኤ ተፈርሞ በሚያዚያ 30 ቀን 2019 ተግባራዊ ሆኗል፤ እ.አ.አ. ከጥር 1 ቀን 2021 ጀምሮ ንግድ እንዲጀመር ስምምነት ላይ ተደርሷል።




# በኢትዮጵያ በዓመት ሰባት ሺህ ሰዎች በቫይረሱ ይያዛሉ



**ማርቆስ በላይ**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- በኢትዮጵያ በዓመት ሰባት ሺህ ሰዎች በኤች አይ ቪ ቫይረስ እንደሚያዙ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በቫይረሱ ምክንያት በዓመት ከ10 ሺህ በላይ ሰዎች እንደሚሞቱ ተገልጿል፡፡

ትኩረቱን በፀረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላይ ያደረገ የማኅበረሰብ መር ክትትል ፕሮጀክት ትናንትና ይፋ ሆኗል።

በጤና ሚኒስቴር የኤች አይ ቪ፣ ሄፒታይተስና አባላዘር በሽታ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ያደታ በመርሐ-ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በዓመት ከሰባት ሺህ በላይ አዲስ ሰዎች በቫይረሱ የሚያዙ ሲሆን፤ ከ10 ሺህ በላይ ዜጎች በየዓመቱ ይሞታሉ።

በመላ ሀገሪቷ የሚገኙ 605 ሺህ ሰዎች የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ይገኛል ተብሎ ይገመታል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ ሥርጭቱ እየቀነሰ መምጣቱን ጠቅሰው፤ አዲስ የሚያዙ ሰዎች እድሜያቸው በአማካኝ ከ15 እስከ 29 መካከል እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የበሽታው ምጣኔ በአዲስ አበባ፣ በጋምቤላ እና በትላልቅ ከተሞች ከፍ ያለ መሆኑን አንስተው፤ እንደአጠቃላይ ምጣኔው ከሀገሪቱ ሕዝብ ከአንድ በመቶ በታች ቢሆንም ሥርጭቱ ቀላል የሚባል ባለመሆኑ ግንዛቤው ላይ ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ቫይረሱን ለመከላከል የኮንዶም ስርጭት ወሳኝ መሆኑን የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ ኮንዶም የመግዛትና የማሰራጨት አቅም ውስን በመሆኑ በተለይ ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑና ትኩረት ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገዝቶ እየተሰራጨ መሆኑን ተናግረዋል።

ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭና ትኩረት ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመንግሥትና በአጋር ድርጅቶች እንደሚገዛ ጠቅሰው፤ ዲኬቲ ኢትዮጵያን ጨምሮ በግል ነጋዴዎች በኩልም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ከታክስ ነፃ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ኤች አይ ቪ ኤድስን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር የቫይረሱ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች የሚሰጣቸውን አገልግሎት ለማጠናከር የሚያስችል መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የጣምራ ለማኅበራዊ ልማት ድርጅት ዳይሬክተር አቶ ብሩክ ይርጋለም በበኩላቸው፤ የፕሮጀክቱ ዓላማ በማኅበረሰብ መር ክትትል የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ የፀረ ኤችአይቪ መድኃኒት ተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ዳሬክተሩ፤ 14 ድርጅቶች በጋራ ሆነው በ12 ክልሎችና ሁለት ከተሞች፣ በ84 ወረዳዎችና 103 ጤና ተቋማት ተግባራዊ ይደረጋል ብለዋል።

ከ47 ሺህ በላይ የፀረ-ኤችአይቪ መድኃኒት ተጠቃሚ ቤተሰቦቻችን የአገልግሎት ፍላጎት ተደራሽ ለማድረግ የሚረዳ ፕሮጀክት መሆኑን አስረድተዋል።

# አገልግሎቱ በሩብ ዓመት ከ11 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አገኘ

## - ከ90 ሺህ በላይ አዳዲስ ደንበኞች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በ2017 በጀት ሩብ ዓመት ከ11 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ። ከ90 ሺህ 570 በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ተጠቃሚ ማድረጉንና ለሦስት ሺህ 376 ዜጎች አዳዲስ የሥራ ዕድል መፍጠሩ ተጠቁሟል።

የአገልግሎቱ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ትናንትና በሰጡት መግለጫ በሩብ ዓመቱ ከኢነርጂ ሽያጭ፣ ከአዲስ ደንበኞች አገልግሎቶች፣ ከማያገለግሉ ንብረቶች ሽያጭ እና ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች 11 ነጥብ 55 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 11 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ገልጸዋል።

የገቢ አፈጻጸሙ ከዕቅዱ አንጻር 97 በመቶ መሆኑን ጠቁመው፤ ከአጠቃላይ ገቢው አንጻር ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብሩ የተገኘው ከኢነርጂ ሽያጩ መሆኑን አንስተዋል።

በተጨማሪ በሩብ ዓመቱ 120 ሺህ አዳዲስ ደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 90 ሺህ 573 አዳዲስ ደንበኞች ተጠቃሚ በማድረግ የዕቅዱን 75 በመቶ ማሳካት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

አጠቃላይ የተቋሙን የደንበኛ ቁጥር ወደ አራት ሚሊዮን 850 ሺህ 800 ማሳደግ እንደተቻለ አቶ መላኩ አስታውቀዋል።

ባለፉት ሦስት ወራት ሰፊ የቅድመ መከላከል ጥገና፣ የአስቸኳይ ጥገና፣ የማሻሻያና መልሶ ግንባታ ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቁመው፤ አዲስ 31 የገጠር ቀበሌዎችን ከዋናው ግሪድ በማገናኘት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 26 የገጠር ቀበሌዎችን በማገናኘት 83 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ አፈፃፀም ማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

የኃይል መቆራረጡን በሚፈለገው ልክ መቀነስ አለመቻሉ፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓቱ ወይም ምላሽ አሰጣጡ ተገልጋዮች በሚጠብቁት ልክ አለመሻሻሉና ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቃቸው በሩብ ዓመቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ያሉት አቶ መላኩ፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በተሠሩ የተለያዩ ሥራዎች ለ3 ሺህ 376 ዜጎች የሥራ ዕድል እንደተፈጠረ ተናግረዋል።



**አቶ መላኩ ታዬ**

በሩብ ዓመቱ የተለያዩ የክፍያ አማራጮችን በማስፋፋት በተለይ የዲጂታል ክፍያ አማራጮችን የሚጠቀሙ ደንበኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ጠቁመዋል።

አቶ መላኩ እንደገለጹት፤ የኢነርጂ ታሪፍ ማሻሻያውን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አንስተው፤ የታሪፍ ማሻሻያው በየአራት ዓመቱ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ ሳለ ላለፉት ሁለት ዓመታት ማሻሻያ አልተደረገም።

ከመስከረም አንድ ቀን 2017 ዓ.ም የጀመረው የታሪፍ ማሻሻያም ጊዜውን ያማከለ፣ ተመጣጣኝ እና የተሻለ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለመስጠት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አንስተዋል።

የኃይል መቆራረጥ ድግግሞሽንና የብልሽት ማስተካከያ ቆይታ ጊዜን የማሳጠር ሥራ መሻሻሉን ተናግረው፤ ይህንንም ይበልጥ ለመቀነስ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረው፤ በተለያዩ አካባቢዎች የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያሻሽሉ በርካታ ፕሮጀክቶችና የእድሳት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሩብ ዓመቱ በተጣሩ የብልሹ አሠራር ጥቆማዎች መሠረት 20 የአገልግሎቱ ሠራተኞችን ተጠያቂ መደረጋቸውን ጨምረው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓለም ያላትን አቅም በጋራ እና በኃላፊነት መንፈስ ማልማት ከተቻለ ከረሃብ ነፃ ዓለም መፍጠር አይከብድም!

ሀገራችን ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን ለመቻል እያደረገች ያለችው ጥረት እና እየተመዘገበ ያለው ስኬት እንደ ሀገር የትናንት የረሃብ ታሪካችንን የሚቀይር፤ ከራሳችን አልፈን ለሌሎች መትረፍ የሚያስችለንን አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር ትልቅ ሀገራዊ መነቃቃት ነው። ይህም ለብዙ ሀገሮች በማሳያነት የሚጠቀስ፣ ተጨባጭ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ መሆንም ችሏል።

ሀገሪቱ ለእርሻ ሊውል የሚችል ሰፊ መሬት፣ ተስማሚ አየርና ውሃ እንዲሁም የሰው ሀብት ባለቤት ብትሆንም፣ እነዚህን አቅሞች አቀናጅቶ ወደ ልማት መለወጥ የሚያስችል ፖሊሲና የመንግሥት ቁርጠኝነት ሳይኖር በመቆየቱና አስተማማኝ ሠላም ማስፈን ባለመቻሉ ለምግብ እህል እጥረት፤ ከዚያም ባለፈ ለረሃብ አደጋዎች የተጋለጥንባቸው ወቅቶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም ።

“በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው በየአስር ዓመቱ በቀጣናው የሚከሰተው ድርቅ፤ የምግብ እህል እጥረት ችግራችንን በማባባስ፤ ለብዙ ዜጎቻችን ሞት እና መፈናቀል ምክንያት ለሆኑ የረሃብ አደጋዎች ተጋላጭ ሲያደርገን ቆይቷል። ይህ ሁኔታ ያደረሰብን ጉዳት እንዳለ ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ በብሔራዊ ክብራችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፎ መኖሩም ይታወቃል።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ለዘለቄታው ለመሻገር ከለውጡ መንግሥት ጀምሮ በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል ከፍ ባለ መነቃቃት እና ቁጭት ወደ ሥራ ገብተናል። ይህን ተከትሎም የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘላቂነት ያላቸው ተከታታይ ሥራዎች እያከናወንን ተጨባጭ ስኬቶችንም እያስመዘገብን እንገኛለን።

ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ሀብታችን የተሠማራበትን ይህንን ዘርፍ ምርታማ ለማድረግ የተጀመሩ ሀገራዊ ጥረቶች ፤ በዘርፉ የተሰማሩ ዜጎችን ሕይወት ከመቀየር ባለፈ፤ በየወቅቱ እየፈተነን ያለውን የረሃብ አደጋ ለዘለቄታው በመሻገር በምግብ እህል ራሳችንን እንድንችል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል፤ ያለንን አቅም ተጠቅመን በዓለም አቀፍ ገበያ ተፎካካሪ እንድንሆን የሚያደርገንም ጭምር ይሆናል።

በግብርናው ዘርፍ ያለንን ሀገራዊ አቅም በሚገባ አውቆ መጠቀምን መሠረት ያደረገው የመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫ፤ የዘርፉን ምርታማነት በጥራት፣ በብዛት እና በዓይነት ማሳደግን፤ ከሁሉም በላይ በምግብ እህል ራሳችንን እንድንችል፤ ከዚያም ባለፈ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ የሚያስችል ራዕይ ያነገበም ነው።

እስካሁን በተከናወነው ተግባርም በበጋ የመስኖ የስንዴ ልማት ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል፤ በዚህም በየዓመቱ ስኬታማ መሆን እየተቻለ ነው፡፡ የመስኖ ልማቱ በሀገሪቱ የሚመረተውን የስንዴ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገው ይገኛል፡፡ አጠቃላይ የስንዴ ልማቱ ከውጪ ይገባ የነበረውን ስንዴ ሙሉ በሙሉ በማስቀረት በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመት ዶላር ማዳን አስችሏል። ምርቱን ከሀገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እያስቻለም ነው፡፡

በሌማት ትሩፋትም ሆነ በአረንጓዴ ዐሻራ፤ እንደ ሀገር በምግብ እህል ራስን ከመቻል ባለፈ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ለማስቻል እየተደረገ ያለው ሀገራዊ ጥረትም፤ አሁን ላይ ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል። ይህም ከትናንት የጠባቂነት የታሪክ ምዕራፍ ወጥተን ሙሉ በሙሉ በራሳችን መቆም እንደምንችል በሚገባ አመላክቷል።

የእርሻ መሬት በማስፋት ብቻ ሳይወሰን የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ላይ ትኩረት ያደረገው የመንግሥት የለውጥ አቅጣጫ፤ በተለይም ሀገር እንደ ሀገር ከምግብ እህል ጠባቂነት ለዘለቄታው እንድትወጣ በማድረግ እንዲሁም ትርፍ በማምረት ከረሃብ እና ከረሃብ ነፃ የሆነች ሀገርን እውን ማድረግ ታሳቢ ያደረገ ነው።

ይህም በብሔራዊ ክብራችን ላይ መጥፎ ጥላ አሳርፎ የኖረውን የረሃብተኝነት ታሪክ በመለወጥ፤ ብሔራዊ ክብራችንን ሙሉ በማድረግ፤ አንገታችንን ቀና አድርገን መጓዝ የሚያስችለን አዲስ የታሪክ ትርክት ለመፍጠር በብዙ ቁጭት የጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ሀገራዊ መነቃቃት አካል ነው።

“ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለም” በሚል መሪ ቃል የተጀመረውን ዓለም አቀፍ ጉባኤ እያስተናገድን ያለነው፣ ከረሀብ ነፃ የሆነች ሀገር ለመፍጠር እያደረግነው ያለው ጥረት ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን እያስመዘገበ ባለበት ሁኔታ በመሆኑ፤ ለእኛ ለኢትዮጵያውን ትልቅ ትርጉም ይሰጠናል፤ ለጥረታችን ስኬት አበረታች የሞራል ስንቅ ይሆነናል።

ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለም ለመፍጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተጀመረው ይህ መነሳሳት፤ ዓለማችን ያላትን አቅም በኃላፊነት መንፈስ በጋራ ማልማት ከተቻለ፤ ያለብዙ ውጣ ውረድ ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም፤ ይህም ለብዙዎች እፎይታ የሚፈጥር፤ ለመጪዎቹ ዘመናት ተስፋም ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መነጣጠል እስከማንችል ድረስ ተዋሕደናል!

ሶሎሞን በየነ

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ የሚሆኑ ብሔር፣ ብሔረሰቦች በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር ናት። ከነዚህ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ውስጥ በሰፊ መልክዓምድር ላይ የሚኖሩና ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ቁጥር ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአማራና ኦሮሞ ብሔረሰቦች ተወላጅ ናቸው። እነዚህ ብሔረሰቦች በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር ከሌሎች ብሔር፣ ብሔረሰቦች ጋር ለዘመናት ተከባብረውና ተደጋግፈው እየኖሩ ያሉ ሕዝቦች ናቸው። ሀገሪቱን በዓለም መድረክ ደምቃ እንድትታይ የሚያደርጉ የየራሳቸው መገለጫ የሆኑ ባሕላዊ እሴቶች፣ ቅርሶች፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ሥነ-ቃል፣ ወግ፣ ዕምነት፣ ዕሴትና ሥነ-ጥበብ ያላቸው ብሔረሰቦች ናቸው።

ከዚህ ባሻገር ሁለቱ ብሔረሰቦች ከሌሎች ብሔር፣ ብሔረሰቦች ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ በተጫወቱት ሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ። የኦሮሞና የአማራ ብሔረሰቦች ከሌሎች እህት ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ፣ የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ቀንዲልና ተምሳሌት ሆና፤ ታፍራና ተከብራ እስከ ዛሬ ድረስ እንድትኖር ያደረጉ የሀገሪቱ የሉዓላዊነት፣ የነፃነት፣ የአልደፈር ባይነት፣ ... ዋልታና ማገር ናቸው። የሀገር መደፈር እንደ እግር እሳት የሚያንገበግባቸው፣ ጥቃት የማይወዱ የነበላይ ዘለቀ፣ ባልቻ አባሳፎ፣ አብቹ፣ አብዲሳ አጋ፣ አሊ በርኬ ... የመሳሰሉ የአርበኞችና የጀግኖች መፍለቂያ ብሔረሰብ ናቸው።

እነዚህ የጀግኖች መፍለቂያ፣ ጀግኖችን ከማፍራት ቦዝነው የማያውቁ ማሕፀነ ለምለም ብሔረሰቦች ከሌሎች እህት ወንድም ብሔረሰቦች ጋር በጋራ በመቆም በየዘመናቱ ቅጥሯን ጥሶ፣ ድንበሯን አልፎ የመጣን ጠላት ሁሉ አንገቱን አስደፍተው፣ አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው፣ “ዳግመኛ አይለመደኝም” አስብለው ወደ መጣበት መልሰዋል። ይህን ደግሞ አይደለም ወዳጆቻችን ጠላቶቻችን አፍ አውጥተው መስክረዋል። አፍ አውጥተው የማይናገሩ ግዑዛን ፍጥረታትም ይመሰክራሉ።

እስኪ ጀግኖቹ የተዋደቁበት የዓድዋ ተራሮች የነ ባልቻና የነ ፊታውራሪ ገበየሁን ጀብድ ይመስክሩ። የማይጨው ተራሮች፣ የዓባይ በረሃ የእነ አብቹን፣ የእነ በላይ ዘለቀን የአርበኞቹን ጀብድ ይናገሩ። የካራማራውን ጀግና አሊ በርኬን ዛሬም የሶማልያ በረሃዎች ያስታውሱታል። የሮም አደባባይ ዛሬም የአብዲሳ አጋን ገድል አትዘነጋውም።

ታሪክ እንደሚያስረዳን፣ መሬት ላይ ያለውም ተጨባጭ ሐቅ እንደሚያሳየን ሁለቱ ብሔረሰቦች በሀገራቸው ክብርና ነፃነት የማይደራደሩ፣ ለጠላት የማይንበረከኩ፣ በአንድነት ቆመው የሀገራቸውን ሉዓላዊነት ያጸኑ፣ ለሀገር ነፃነት በየዓውደ ውጊያው በአንድ ምሽግ የወደቁ ብሔረሰቦች ናቸው። የሁለቱም ሆነ የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ኅብረት የኢትዮጵያ የአልደፈር ባይነቷ ሚስጥር ነው።

ይህንን የኢትዮጵያ የአልደፈር ባይነት ምስጢር የተረዱት የሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች፤ የበሬ ወለደ ትርክት በመፍጠር በብሔረሰቦች በተለይ በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል ለዘመናት የልዩነትና የጥላቻ ግንብ እየገነቡ ይገኛሉ። ለዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ የኖሩ ሕዝቦች እንዲገፋፉ ማድረግ የሴራቸው መዳረሻ አድርገው ይዘዋል። ይህንን ለማስፈፀምም የሀገራችንን አንዳንድ ፖለቲከኞችን ሲጋልቡ ይስተዋላል፡፡

በእርግጥ ፖለቲከኞች የተሻለ ርዕዮተ ዓለም ቀርፀው ተፎካክረው ሥልጣን መያዝ በሕግ ተደንግጎ የተሰጣቸው መብት ነው፡፡ ሀገርና ሕዝብን የሚጠቅም፣ ልማትን የሚያፋጥን፣ እድገትንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ፣ ድህነትን ድል የሚነሳ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፈው መወዳደር ያቃታቸው አንዳንድ ፖለቲከኞች ሕዝብን ከሕዝብ የሚለያይ፣ አንዱ ብሔር በሌላው ብሔር ላይ እንዲነሳ፤ የጥላቻ መርዝ ሲረጩ፣ ሥልጣን በቋራጭ ለመያዝ በህቡዕ የታሪካዊ ጠላቶቻችን አጀንዳ ሲያስፈፅሙ ይስተዋላል።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን በተለይ ሰፊ የቆዳ ስፋትና ሕዝብ ያላቸው ሁለቱ ብሔረሰቦች በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎና ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ይረዳሉ። ሁለቱ ሕዝብ በዓይን ጥቅሻ ሲግባቡ፤ ከፊታቸው የሚቆም ጠላት እንደማይኖርና የትኛውም ችግር እንደማይበግራቸው ጠንቅቀው ያውቁታል። በሀገሪቱ ለመጣው ለውጥ የኦሮ-አማራ ጥምረት ጉልህ ድርሻ መኖሩን ያስታውሱታል። ስለዚህ የሁለቱ ብሔረሰቦች አንድ መሆን፤ ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የታሪካዊ ጠላቶቻችን አጀንዳ አስፈጻሚ አንዳንድ ፖለቲከኞቻችንን እንቅልፍ ነስቷቸዋል።

ታዲያ ከሰሞኑ የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች የፖለቲካ አዋቂ ሰዎች “ፖለቲካል ኢሊትስ” በሀገረ አሜሪካ ተገናኝተው መወያየታቸውን ተከትሎ፤ አንድ ተምሮ ያልተማረ ምሑር ነኝ ባይ፣ የታሪካዊ ጠላቶቻችን ፍርፋሪ ለቃሚ ከወደ ዋሽንግተን “የአማራና የኦሮሞ ብሔረሰብ ጥምረትን በማንቋሸሽ የጥላቻ መልዕክት አስተላልፏል።

ይህ ሰው ፕሮፌሰር የሚል ማዕረግ ተሰጥቶታል እንጂ፤ እንደኔ አይደለም፡፡ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ መመረቅ ይቅርና ፊደል የቆጠረ አይመስለኝም። ምክንያቱም ሰውየው በስደት የሚኖርባት ሀገረ አሜሪካ ዛሬ ላይ በሁሉም ነገር የዓለም ቁንጮ ለመሆን የበቃችው፤ በ54ቱም ግዛቶቿ የሚኖሩ ሕዝቦቿ ልዩነትና መከፋፈልን ወደጎን ብለው አንድነትን በመምረጣቸው ነው። በአንድነት፣ በኅብረት፣ በተሠራች ሀገር ላይ ተደላድሎ ተቀምጦ፤ ሳይማር ያስተማረውን ሕዝብ ከፋፍሎ ለተኩላ ለመስጠት ከሚሠራ በላይ ቂል ያለ አይመስለኝም።

ሰውየው በንግግሩ የታሪክ ድሃ መሆኑን በግልፅ አሳይቷል። ለአብነት ዓድዋ ላይ “ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ” ተብሎ የተገጠመው ፊታውራሪ ገበየሁ ቢሰዋ፤ ባልቻ አንድ ስንዝር እንኳን ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ልቡ አላመነታም። ይልቁንም መድፍ ብቻውን እያገላበጠ ከወንድሙ ገዳዮች ጋር አንገት ለአንገት ተናንቆ ወንድሙ የተሰዋለትን የሀገሩን ነፃነት አስከበረ እንጂ። ታዲያ ከዚህ በላይ ጥምረት፣ ፍሬ፣ ውሕደት፣ ኅብረት ... ከወዴት አለ?

ከዓድዋው ሽንፈት ከ40 ዓመት በኋላ ዳግም የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ወሮ በቆየበት አምስት ዓመት ውስጥ፤ የሁለቱ ብሔር ተወላጅ ጀግኖች አርበኞች እነ በላይ ዘለቀ፣ አብቹ ... ከሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች ጋር ተናበው ጠላትን መቆሚያ መቀመጫ አሳጥተው፣ ዶጋ አመድ አድርገው ዳግም አንገቱን አስደፍተው ወደመጣበት የሸኙት። ታዲያ በአንድነት ቆሞ የሀገርን ነፃነት ከማስጠበቅ በላይ ምን ፍሬ አለ?

ደግሞስ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ አንዱ የአንዱን ቋንቋ፣ ባሕል፣ ወግ ወርሶ ተጋምዶ እየኖሩ ካሉ ከነዚህ ብሔረሰቦች ሕዝብ በላይ ምን ዝምድና፣ ኅብረት፣ ፍሬ፣ አለ? እስኪ ንገሩኝ በአንድ ኩንታል ውስጥ ተቀላቅሎ ያለን ነጭና ጥቁር ጤፍ፤ ጥቁርና ነጩን ለየብቻ መለየት የሚቻለው ማነው? ማንም ነጩን ለብቻ፣ ጥቁሩን ለብቻ መለየት አይችልም። በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ተጋብቶ ተዋልዶ የሚኖረውን የአማራና የኦሮሞ ብሔረሰቦችን ሆነ ሌሎችን ብሔረሰቦች ማንም መለየት መነጣጠል አይችልም።

ለጊዜው በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ለዘመናት ተከባብረውና ተደጋግፈው የሚኖሩ ብሔረሰቦችን ለመከፋፈል በሚጎነጎነው ሴራ ፈተናው ሊበረታ ይችላል። ዳሩ ግን ከኅብረትና ከአንድነታቸው የሚለያቸው ማንም የለም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ያለን ብሔር ብሔረሰቦች መነጣጠል እስከማንችል ድረስ ተዋሕደናል!

በመሆኑም በውጭም በሀገር ውስጥም ያላችሁ ተማርን የምትሉ ሰዎች ሳይማር ያስተማራችሁን ማኅበረሰብ አዳዲስ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ፈጠራ በማፍለቅና በማሸጋገር ሕዝብና ሀገርን መጥቀም ካልቻላችሁ፤ ቢያንስ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ ተስማምቶ በሠላም ከሚኖረው ሕዝብ እጃችሁን አንሱ። ቸር ሰንብቱ!

# ተጠየቅ

# ‹‹በምንሰራው የጥራት ናሙና ላይ የሚቀርበው ቅሬታ ከአንድ ፐርሰንት በታች ነው››

- አቶ በኃይሉ ንጉሴ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገበያና ግብይት ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ

መክሊት ወንደሰን እና ሞገስ ተስፋ

**የገበያ ትርጉም በተለምዶ ሰዎች ምርታቸውን በመሸጥ የሌላቸውን ምርት የሚሸምቱበት መንገድ ነው:: የተለምዷዊ ግብይት ስርዓት በዘመናዊ መንገድ ግብይት ሲከናወን ለህዝብም ሆነ ለሀገር ጥቅሙ ላቅ ያለ ነው:: መንግስት ተለምዷዊ የሆነውን የግብይት ስርዓት በዘመናዊ መንገድ መምራት ያስችለው ዘንድ የኢትዮጵያ ምርት ገበያን በአዋጅ ቁጥር 550/1999 በድጋሚ በ1050/2009 አሻሽሉ አቋቁሟል::**

**ተቋሙ በውድድር ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የሆነ የግብይት ስርዓት የመዘርጋት፤በሀገር ደረጃ የሚመረቱ የግብርና ውጤቶችን በተደራጀና ስርዓት፤ምርቶችን ተረክቦ፤ ደረጃ አውጥቶ፣ ከዝኖ፣ ሽጦ ገንዘቡን ለባለቤቱ የማስረከብ ኃላፊነት የተሰጠው፤በዚህም ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ እያደረገ ያለ ነው።**

**የዝግጅት ክፍላችን ተቋሙ የተሰጠውን ኃላፊነት በመወጣት አኳያ የት ጋር ነው ? እስካሁን ባለው የስራ አፈጻጸም ለሀገርስ ምን ጥቅም አስገኘ? ግብይት ስርዓቱን ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ፤ የግብይት ስርዓቱ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮች ምንድን ናቸው?፤ በተለይ በቡና ምርት እና በጥራጥሬ ምርቶች ግብይት ውስጥ ያለውን ችግር በምን መልኩ እየተፈታ ነው? በሚሉና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ የምርት ገበያ የገበያና ግብይት ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በኃይሉ ንጉሴ አነጋግሮ፤ ምላሻቸውን እንደሚከተለው አቅርቦታል::**

**አዲስ ዘመን፦ ተቋሙ በአዋጅ የተቀመጡለትን ኃላፊነቶችን ከመፈጸም አንጻር ምን ደረጃ ላይ ነው?**

**አቶ በኃይሉ፦** በአዋጁ ተቆጥረው የተሰጡንን ስራዎች እያከናወነውን ነው:: ገበያውን ከእጅ በእጅ ግብይት ወደ ቴክኖሎጂ የታገዘ ግብይት የማሸጋገር ስራንም በሙከራ ደረጃ ፓይለት አድርገናል:: እሱን ለማሳደግ ጠንክረን መስራት አለብን ብለን በ2017 ዓ.ም እቅዳችን ላይ ይዘነዋል:: ይህንን የወደፊት ግብይትን ማጥናት፣ አዋጭነቱን ማጥናት እንዲሁም ተግባራዊነቱን ማጥናት አለብን የሚለውን በእቅዳችን ላይ ይዘን እየሰራን ነው:: ተጠሪነታችን ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እንዲሁም ለፓርላማ እና ንግድና ቱሪዝም ቋሚ ኮሚቴ ነው:: በየጊዜው ሪፖርቶችን እየላክን ይገመገማል፤ ግብረመልሶችን እናገኛለን:: ከሞላ ጎደል መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው ተቋሙ በተልዕኮ የተሰጠውን እየፈጸመ ነው::

በአዋጁ ላይ በግልጽ የተሰጠን በውድድር ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የሆነ የግብይት ስርዓት መዘርጋት ነው:: ገበያው ሲጀመር የቀን ማስተጋባት ወይም ማስነገር የግብይት ስርዓት የሚባል ነበር:: ብዙ ገዥዎችና ብዙ ሻጮች መድረክ ላይ ተገናኝተው ዋጋቸውን፤ የምርታቸውን አይነት፤ ምርት የሚገኝበትን ቦታ እየጠቀሱ ድርድር የሚያደርጉበት፤ በአካል ተገናኝተው የሚገበያዩበት የግብይት ስርዓት ነበር:: ምርት ገበያው ያንን የግብይት ስርዓት ለስምንት ዓመታት አካባቢ ሲጠቀምበት ቆይቶ አሁን ወደ ኢሌክትሮኒክ ግብይት ስርዓት ማሸጋገር ችሏል:: ይህ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ስርዓት ድሮ ሰዎች በአካል ተገናኝተው የሚያደርጉትን ግብይት ከኮምፒውተር ላይ ቁጭ ብለው ግብይት የሚያደርጉበትን የግብይት ስርዓት መዘርጋት ችለናል:: ዲጂታላዜሽን እንደ ሀገር ስትራቴጂ ሆኖ እየሰራንበት ያለ ስራ በመሆኑ የኦንላይን የግብይት ስርዓት ለምቶ በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን፦ ግብይቱን ከማዘመን አንጻር የተመዘገቡ ስኬቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ በኃይሉ፦** ከስኬቶቹ መካከል አንዱና ዋነኛው ዘመናዊ ግብይትን በራሱ ማንበር ወይ መፍጠር እና ማዝለቅ አንዱ ነው:: በሌሎች ሀገራት ሲታይ ምርት የሚከዝን፤ ጥራት የሚያወጣ፤ ገበያ፤ ተገበያዩም ክፍያ የሚፈጽምበት የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጀቶች አሏቸው:: በኢትዮጵያ ምርት ገበያ እነዚህ ተቋማት በሌሉበት የተፈጠረ ተቋም ነው:: ምርቶችን ተረክቦ፤ ደረጃ አውጥቶ፣ ከዝኖ፣ሽጦ ገንዘቡን ለባለቤቱ ማስረከብ፤ይህንን ችግሮች ሳይከሰቱ ማሳካት እንደ ስኬት የሚወሰድ ነው:: ከአዲስ አበባ በአንድ መጋዘን ተነስተን ዛሬ ላይ በሀገሪቱ 25 ቦታዎች ላይ አገልግሎት የምንሰጥባቸው መጋዘኖችና ቢሮዎች ተዘጋጅተዋል:: ሁለት ቦታዎች ላይ ደግሞ ሌሎች የግብይት አማራጭ ለሚያስፈልጋቸው ምርቶች የምድር ሚዛን አገልግሎት የምሰጥባቸው መጋዘኖች ተደራጅተዋል::

ከግብይትም አንጻር ሲታይ ግብይት አዲስ አበባ ላይ በዋና ቢሮ የተጀመረ ነበር:: አሁን ላይ ግን በስድስት ቦታዎች ላይ ልክ እዚህ አዲስ አበባ እንዳለው ሆኖ ግብይት የሚካሄድበት ስርዓት መፍጠር ተችሏል:: ከምናገበያያቸው ምርቶች አንጻር እንደ ስኬት ሊቆጠር የሚችለው ብዝሃ ምርቶችን ወደ ግብይ ስርዓት ማምጣታችን ነው:: እነዚህ ምርቶች ደግሞ ለውጭ ገበያ የሚውሉ ናቸው:: እንደ ሀገር የግብይት ስርዓት መፍጠር የገበያ መሰረተ ልማት የሚባለው ከ‹‹ሀረድዌሩ›› ባለፈ ‹‹ሶፍትዌሩ›› የሰው ኃይል ላይ ዘመናዊ ገበያ ያስፈልጋል የሚለውን አመለካከት መቅረጽ አስፈላጊ ነው::

እስካሁን የምናገበያየው የግብርና ምርቶችን ሲሆን አሁን ላይ የኢንዱስትሪ ምርቶች ለማገበያየት ውይይቶች እየተደረጉ ነው:: ምርት ገበያ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ መረጃዎች ተደራጅተው ተቀምጠዋል:: ይህ መሆኑ ለምርምር፣ ለፖሊሲ ጥናት ይሁን ትልቅ አቅም አለ:: ገበያው በራሱ የቆመ አይደለም:: የተፈጠረው ስነምህዳር ነው:: ይህም ምርት ክምችትን ከምርት ግብይቱ፤ ምርት ክምችቱን ከፋይናንስ ስርዓቱ እና ከታክስ ስርዓቱ ጋር እንዲገናኝ ተደርጓል:: በእኛ ግብይት ስርዓት ውስጥ መጥቶ የሚገበያዩ ምርቶች ታክስ ይሰበስብባቸዋል::

እስካሁን ባደረግናቸው ግብይቶች ወደ 18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ታክስ ለሚመለከተው አካል ማስገባት ችለናል:: አቅምን ለማሳደግ ደግሞ የምርት ገበያ አካዳሚ ገንብተናል:: አካዳሚው ለምናገበያያቸው ምርቶች በኢንዱስትሪ ላይ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመድፈን በተለያዩ መስኮች ስልጠናዎችን እንሰጣለን:: የቡና ቅምሻ ስልጠና፤ የጥራጥሬና ቅባት፤ የምርት ጥራት ምደባ፤ የኤሌክትሮ ግብይት ስልጠና እንሰጣለን:: አካዳሚው ለሌሎች ሀገራትም ጭምር ስልጠና እየሰጠ ነው:: ግብጽ፤ ኬንያ፤ አንጎላ፤ ሞዛምቢክና መሰል የአፍሪካ ሀገራት እስከ 10 ሺ ዶላር ከፍለው ስልጠና ወስደዋል:: ቆዳና ሌጦ ላይ ጥናቶች ተሰርተዋል:: አቅም ከመገንባት አንጻር ከ8 ሺ በላይ ወጣቶችን አሰልጥኖ ወደ ስራ አስገብቷል:: ገበያዎች ላይ ብዙ ወጣቶች ስራ ላይ ናቸው::

**አዲስ ዘመን፦ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በቡና ምርቱ ምን ያህል ቶን ግብይት ተፈጸመ?**

**አቶ በኃይሉ፦** በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 20 ሺ ሜትሪክ ቶን የሚሆን የቡና ግብይት ተፈጽሟል:: ከተደረገው ግብይት ከፍተኛው የሀገር ውስጥ ግብይት ነው:: የሀገር ውጭ የቡና ግብይት ላይ በገጠመን ችግር ምክንያት አቁመን ነበር:: ችግሩን ለመፍታት ከግብርና ሚኒስቴር እና ከንግድና ቀጠናዊ ሚኒስቴር ጋር ተነጋግረን አቅጣጫ ተቀምጧል:: በሚቀጥሉት ቀናት የኤክስፖርት ቡና ግብይት በሰፊው ይደረጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

**አዲስ ዘመን፦ የሀገር ውጭ የቡና ግብይቱ እንዲቆም የተደረገበት ምክንያት ምን ነበር?**

**አቶ በኃይሉ፦** የቡና ግብይት የሚገበያይበት አውድ ከሌሎቹ የተለየ ነው። የተለየ የሚያደርገው የቡናና ሻይ ባለስልጣን የሚያስቀምጠው የቡና ዋጋ ገደብ አለ:: የቡና ዋጋ ገደብ ለምን መጣ? ከተባለ በግብይት ስርዓት ውስጥ ያለው አንድ ችግር ምርቶች በሀገር ውስጥ የሚገዙበት ወይም የሚሸጡበት ዋጋ እና ወደ ውጪ የሚሸጥበት ዋጋ የተናበበ አልነበረም:: የዚህ መሰረታዊ ችግር የእኛ የውጭ ምንዛሬ ወይንም ‹‹ፎርኤክስ›› ለገበያ የተለቀቀው ትክክለኛ ‹‹ቫሊው›› የተደረገ አልነበረም:: በዚህ ምክንያት በተለይ ላኪዎች ቡናን ወይም ሌሎች ምርቶችን ሀገር ውስጥ በከፍተኛ ዋጋ ይገዙና ከሀገር ውጭ ሲሄዱ የሚሸጡት በዝቅተኛ ዋጋ ነው:: ያንን ኪሳራ ለማጣራት ወደ ውጭ በሚልካቸው ምርቶች ላይ ዋጋ እየጨመሩ ትርፋቸውን ሲያጣሩ ነበር::



ላለፉት ዓመታት ስንቸገርበት የነበረው አንዱ ነገር ምርቶች የሚገበያዩት በትክክለኛ ዋጋቸው አልነበረም:: ስለዚህ ከዛ ጋር ተያይዞ ቡና እና ሻይም ምርቶች በከፍተኛ ዋጋ ነው የሚሸጡት ስለሚባል የቡና ዋጋ ይሰጠን ነበር:: የቡና ዋጋ ከዚህ ውጪ ካልሆነ እንዳታገበያዩ በሚል ባለስልጣኑ ዋጋ ተምኖ ይሰጠን ነበር:: ሌላው የነበረው ችግር የሚተመነው የቡና ዋጋ ትክክለኛ ዋጋው አልነበረም::

ምክንያቱም ሰዎች ወደ እዚህ ገበያ እየመጡ አልነበረም:: ሌሎች አማራጭ የግብይት ስርዓቶች ስለነበሩ እዛ ሄደው ግብይት ያደርጋሉ:: በቅርቡ በተደረጉ ንግግሮች የግብርና እና የንግድና ቀጠናዊ ሚኒስትሮች አቅጣጫ አስቀምጠውልናል:: ከኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ጋር ተነጋግረን ለገበያው የቀረበ የቡና ዋጋ ደረጃ ተቀምጦ ግብይቶች የሚጀመሩበት አግባብ በዚህ ሳምንት ተግባራዊ ይሆናል:: ስለዚህ ያለው ችግር ከሞላ ጎደል ተቀርፏል ማለት እንችላለን::

**አዲስ ዘመን፦ በተያዘው በጀት ሩብ ዓመት ላይ የውጭ ሀገር የምርት ገበያ አለመኖሩ ምን ክፍተት ፈጠረ?**

**አቶ በኃይሉ፦** እንደገበያ የምናገበያያቸው ምርቶች ቀንሰዋል:: ነገር ግን ያለን አቋም አማራጭ የግብይት ስርዓቶች መኖር አለባቸው የሚል ነው:: ሰዎች በአንድ የገበያ አማራጭ ብቻ መገደብ የለባቸውም:: ይህ ገበያ ሲቋቋም ሁሉም ምርቶች በአስገዳጅነት የሚገቡበት የግብይት ስርዓት ነበር:: ነገር ግን ከጊዜ ወደጊዜ የተገበያዮች ፍላጎት ታክሎበት መንግስት አማራጭ የግብይት ስርዓቶችን ዘርግቷል:: እኛ ደግሞ እነዛን የግብይት ስርዓቶች እንዲዘረጉ የራሳችንን አበርክቶ አድርገናል:: ለምሳሌ ኢትዮ ቴሌኮምን በጣም ያበረታው የሳፋሪኮም ወደ ውድድር መምጣቱ ነው::

ስለዚህ የምናስበው የውድድር መንፈሱ ይፈጠራል፤ ከአማራጭ የግብይት ስርዓቶች ጋር ተወዳድረን ለማሸነፍ ጠንክረን እንሰራለን:: በአጋጣሚ አሁን ላይ የተፈታው እና ትክክል ያልነበረው በባለስልጣን መስሪያ ቤት እየተተመነ የሚላከው እና የሚሰራበትም መንገድ ትክክል ስላልነበር የተፈታበት መንገድ አለ:: ምርት ገበያውም ተወዳድሮ በአገልግሎት አሰጣጡ ተመራጭ ሆኖ፣ ደንበኞችን ስቦ ለደንበኞች የተቀላጠፈ ወጪ ቆጣቢ የሆነ የግብይት አገልግሎት በመስጠት ማሸነፍ አለበት ብለን ስለምናስብ ባለፉት ዓመታት የነበሩበት ነገሮች ከዚህ በኋላ ለምንሰራው ስራ ትምህርት ሰጪ ናቸው:: ወደ ኦንላይን ለመውጣት ያሰብነው ከእነዚህ ትምህርት በመነሳት ነው::

ከማገበያየት አንጻር ከፍተኛ የሆኑ ምርቶች በሌሎች አማራጭ የግብይት ስርዓቶች እየተገበያዩ ነው:: ነገር ግን እንደሀገር እስከመጨረሻው ዓላማችን አንድ ነው:: በማንኛውም መንገድ ብንሄድ እነዚህ ምርቶች ተወዳዳሪ ሆነው በጥራት ተመርተው ዓለም ገበያ ውስጥ ገብተው አሸንፈው ለሀገር የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እስካመጡ ድረስ በተፈጠረው ስነ-ምህዳር ውስጥ እኛ የምንጫወተው ሚና አለ:: ለአብነት ብንጠቅስ እኛ ጋር ባይገበያዩም እነዚህ ምርቶች ሲመጡ የጥራት ደረጃ ሰርተፍኬት ልንሰጥ እንችላለን፣ የምድር የምርት ምዘና አገልግሎት ልንሰጥ እንችላለን፣ ምርቶቹን ማስቀመጥ ለሚፈልጉ ደግሞ የመጋዘን አገልግሎት እንሰጣለን:: ስለዚህ በዚህ ውስጥም ሚና አለን:: ነገር ግን እንደ አጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ስናገበያየው ከነበረው መጠን አንጻር ሲታይ ቅናሽ አሳይቷል:: ይህ እንደ አንድ ክፍተት የሚታይ ነው::

**አዲስ ዘመን፦ በአሁኑ ወቅት ተጥሉ የነበረው የቡና መገበያያ ተመን ሙሉ በሙሉ ተነስቷል? ከዚህ በኋላስ ትክክለኛ ተመን እንዲወጣ ለማድረግ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ በኃይሉ፦** አሁን ተመኑ በትክክለኛው መንገድ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹በምንሰራው የጥራት ናሙና ላይ...



**ከ6ኛ ገፅ የዞረ**

እንዲተመን ካለፈው ሳምንት ጀምሮ አቅጣጫ ተቀምጧል። ይህ ተመን ከዚህ ሳምንት ጀምሮ ተግራዊ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ተመኑ የሚሰራው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ነው። ለምሳሌ በዓለም ላይ ዛሬ ቡና የሚገዛበት ዋጋ ይታወቃል። ሂሳቡን የሚሰራው ኔትዎርክ ላይ ነው። ኢትዮጵያ ላይ ቡና በስንት አካባቢ መሸጥ አለበት? ብሎ ተቀናሽ የሚሆኑ ወጪዎችን ቀንሶ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የሚኖረውን ተመን ይዞ ነው። ስለዚህ የምናስበው ተመኑ ማንም ተመነው ማንም በቀመር የሚሰራ ስለሆነ ትክክለኛ ተመን ይሆናል ብለን ነው።

እንደ ሀገር የውጭ ምንዛሬ ማሻሻያ ‹‹ሪፎርሙ›› ከታች እስካለው ገበሬ ድረስ መውረድ አለበት የሚል አቅጣጫ ተቀምጧል። ስለዚህ ይህንን ለማሳካት የተያዘ ስለሆነ በቅርበት ከቡና እና ሻይ ባለስልጣን ጋር በጋራ በመስራት ችግሩን ለመፍታት አቅጣጫ ተቀምጧል።

**አዲስ ዘመን፡- የኒውዮርክ ገበያን በመመልከት ዋጋ እንደምታወጡ ይታወቃል፤ የኒውዮርክ ገበያ ብዙ ጊዜ በካፒታሊስት ባለሀብቶች የሚመራ ነው። ከዚህ አንጻር ጥቅም እና ጉዳቱን እንዴት ይገልጹታል? የኒውዮርክን ገበያ መሰረት ከማድረግ ውጭስ ሌሎች አማራጮች አሉ?**

**አቶ በኃይሉ፡-** ኒዮርክ ላይ የሚደረገው ገበያ ዋጋ አመላካች ነው። ይህም ማለት ኒዮርክ ላይ የሚደረገው የቡና ገበያ አንዱ ‹‹ፊውቸርስ›› የሚባል ገበያ ነው። ‹‹ፊውቸርስ›› ኮንትራት ማለት፤ እኛ የምናገበያየው እጅ በእጅ ነው። ምርት፤ ገንዘብ ስለሚኖር እንቀያየራለን። ኒዮርክ ላይ ግን ኮንትራት ይኖራል፤ ያን ኮንትራት መልሶ መሸጥ ይቻላል። ምርትን የማስረከብ ግዴታ አይጣልም።

የኒዮርክ ገበያ ግብይት ዛሬ ተፈጽሞ የሚደርሰው ከሁለት ወይም ከሶስት ወር በኋላ ነው። አመላካች ነው ያልኩበት ምክንያትም አሁን ጥቅምት ላይ ነው ያለነው፤ ታህሳስ ወይም ጥር ላይ የዓለም የቡና ዋጋ ወዴት ሊሄድ ይችላል? የሚለውን ትክክለኛውን ሳይሆን አመላካች የሆነውን ዋጋ ይሰጠናል።

በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ ትልቁ ጥቅም የሚሆነው እኛ የምናመርታቸው ምርቶች በጣም በርካታ የሆነ ‹‹ስፔሻሊቲ›› ቡናዎችን ስለሆነ የሚተመኑት በኒዮርክ ገበያ አይደለም። የሚወጣው ከገዢ ሀገር ነጋዴ ጋር እርስ በእርስ በሚደረግ ተመንና ድርድር ነው። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ቡና በጣም ተወዳዳሪ ከማድረግ አንጻር ከኒዮርክ በጣም ከፍ ባለ ዋጋ መሸጥ ያስችላል። ጥራታቸው ዝቅ ያሉ ከኒዮርክ ዋጋ ዝቅ ባለ ዋጋ ግብይት የሚደረግበት አውድ አለ። ለሌሎች ምርቶች እንዲሁ አመላካች ገበያዎች አሉ። ሰሊጥ ህንድ፤ ቻይና ይገዛሉ። በሀገራቱ አካባቢ ያለው ዋጋ ለእኛ ምልክት ይሆነናል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሰሊጥ በትክክል ስንት ይገባዋል? ቢባል ሰሊጥ ከሌሎች ሀገራት ሰሊጥ ጋር ጥራቱ እኩል አይደለም። የራሳችን የሆነ የመወዳደሪያ ዕድል ስላለን ላኪዎቻችን የሚደራደሩት ያንን ይዘው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ከብዙ አምራች ሀገራት በተሻለ ተወዳጅ ቢሆን ከአመራረት አሰባሰብ ሂደቱ ጋር በተገናኘ በሚፈጠሩ የጥራት ችግሮች የሚሸጥበት ዋጋ ዝቅተኛ ነው። ችግሩን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ በቅንጅት ከመስራት አኳያ ምን ታስባል?**

**አቶ በኃይሉ፡-** ይህንን ጥያቄ በተመለከተ ከእኔ በተሻለ የቡና እና ሻይ ባለስልጣን ቢመልሰው ይሻላል። ምክንያቱም የቡና እና ሻይ ከማስመረት ከሀገር ውጭ እስከመሸጥ ያለውን አጠቃላይ የግብይት ሰንሰለት የሚቆጣጠረው እሱ ነው። ነገር ግን እኔ ከጥራት አንጻር በተለይ የምርቶችን ጥራት ከማሳደግ አንጻር አንድ የምናደርገው ነገር ለምርቶች ደረጃ እንሰጣለን።

ለምሳሌ የቦንጋ ምርት ሲመጣ የምርት ጥራት ደረጃ እናወጣለን። ደረጃ የምንሰጠው ቦንጋ አካባቢ ያመረቱ ወረዳዎች ያገኙት የምርት ጥራት ደረጃ ምን እንደሚመስል ግብረመልስ በመስጠት ነው። የምርት ጥራት ደረጃ እየተሻሻለ ነው ወይም ዝቅ እያለ ነው የሚል ግምገማ ይደረጋል።

**አዲስዘመን፡- ምርት ገበያን በእጅጉ ይፈትኑታል የሚባሉት የጥራት ደረጃ አሰጣጥ ላይ የሚስተዋል ሙስና ነው ይባላል፤ ችግሩን ለመከላከል ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ በኃይሉ፡-** እንግዲህ ጥራት አስቸጋሪ ነገር ነው። እንደፍልስፍና የምናስበው ብዙ ሰው ላመረተው ምርት ትክክለኛ የሆነ የጥራት ደረጃ ይዞ ትክክለኛ የሆነ ዋጋ ለማግኘት ይሰራል ብለን ነው። ነገር ግን ግብይት ስርዓቶች ውስጥ ሌሎች ነገሮች ውስጥ እንዳለው ሁሉ አንዳንድ ሰው ደግሞ በራሱ በትክክለኛው መንገድ ያላገኘውን ለመጠቀም የሚፈልግ ይኖራል። ይህ ተግባር ደግሞ የእኛን ሲስተም ይፈትናል። በጥራት ደረጃ አሰጣጥ ውስጥ የሚኖሩ ችግሮች ይኖራሉ። ነገር ግን አንዱ እና ዋነኛው ጉዳይ አሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው።

የአሰራር ስርዓቱ አንድ የምርት ገበያ ላይ አንድ ሰው ምርቱን ይዞ ሲመጣ ተመዝግቦ ከምርቱ ናሙና ይወሰዳል። ናሙናው ሲወሰድ ናሙናውን የሚወስዱት አካላት ወደላቦራቶሪ ሲልኩ የማን እንደሆነ አይታወቅም። ልክ ደም ስንሰጥ በኮድ ተወስዶ ላቦራቶሪ ቴክኒሻኑ እንደሚመረምረው ኮድ ያደረግና ላቦራቶሪ ውስጥ ይገባል። ላቦራቶሪ ውስጥ የሚሰራው አንድ ሰው አይደለም። ፓናል ተደራጅቶ የሚከታተል ልምድ ያለው እና አባላት ያሉት ነው። በዚህ ጥረት ትክክለኛውን የጥራት ደረጃ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል። አምራች ወይም ላኪ የጥራት ደረጃው ከተሰጠው በኋላ አቤቱታ ያቀርባል። ይህ ትክክለኛ አይደለም የሚልበትን አግባብ ግብረ መልስ የሚሰጥ ቡድን አደራጅተናል።

አንድ አምራች ቅርንጫፍ ላይ ምርትህ ደረጃ ሶስት ነው ሲባል፤ ምርቴ ደረጃ ሁለት ነው የሚል ከሆነ ደረጃ ሁለት መሆኑንና አለመሆኑን ድጋሚ ይፈተሻል። ካልተፈታ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት ተልኮ ይመረምራል። ከዚያ ባሻገር ከሆነ ሌሎች ገለልተኛ ተቋማት መርምረው የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። ከምንሰራው ናሙና የሚቀርበው ቅሬታ ከአንድ ፐርሰንት በታች ቢሆንም አንድም ቅሬታ ቢሆን በትክክል መሰራት አለበት።

ከሙስና ጋር ተያይዞ እንዲህ አይነት ነገሮች በተጨባጭ መረጃዎች በእራሳችን ‹‹ኢንተለጀንስ›› እና በሰዎች ጥቆማ ካገኘን እርምጃ እንወስዳለን። እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ ምንም ትግስት አናደርግም። ይህንን ለመስራት የክልል ቢሮዎችን ያካተተ የስነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚቴ አለ። የአገልግሎት መስጫዎችን የተቀመጡ ሲሆን በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ ቅሬታ የሚቀበሉ አሉ። እንደዚህ አይነት ጥቆማዎችን እየወሰድን በተቻለ መጠን የእርምት እርምጃዎችን እንወስዳለን፤ ችግሩም እንዳይንሰራፋ ስራዎችን እየሰራን ነው። ከዚህ ቀደም በጣም ብዙ እርምጃዎችን ወስደናል። ብዙ ማሻሻያዎችንም አድርገናል። በቅርቡም ከዋና መስሪያ ቤት ጀምሮ እስከ ቅርንጫፎች ድረስ ትልቅ ማሻሻያ አድርገናል። በርካታ ሰራተኞችንም ቀይረናል።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ከማዘመን አኳያ ምን እየሰራ ነው?**

**አቶ በኃይሉ፡-** የምንሰጠው አገልግሎት የግብይት አገልግሎት ነው። በዚህ አገልግሎት ላይ በቃል ከማስተጋባት ወደ ኤሌክትሮኒክ እንዲሄድ አድርገናል። አሁንም ከኤሌክትሮኒክ ወደ ኦንላይን እንዲያድግ ተደርጓል። ከተደራሽነት አንፃር አዲስ አበባ ስንሰራ የነበረውን ስራ ወደ ስድስት የክልል የገበያ ማዕከላት አሳድገናል። ከግብይት ሞዴል አኳያ የነበረን አንድ ሞዴል ነበር። አሁን ወደ ሶስት ሞዴል ማሻሻል ችለናል። ሌሎችም የሚመጡ ምርቶች ሲኖሩም እንደ ባህሪያቸው እየታየ ሌሎች ሞዴሎችን እንፈጥራለን።

በመጋዘን አገልግሎት ላይ የሚዛን አገልግሎታችንን ዘመናዊ ለማድረግ ዲጂታል ሚዛኖችን የመግጠም ስራ ተሰርቷል። የእኛ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በሌሉበት ቦታዎች የሚዛን አገልግሎት ለመስጠት የሳተላይት ቅርንጫፎችን የማደራጀት፤ የምርት የጥራት ደረጃዎችን ለማሻሻል በተለይ በላብራቶሪ ውስጥ የሚሰሩ የሰው ኃይል እና መሳሪያዎችን በማደራጀት የመረጃ ቅብብሎሹንም ለማዘመን በርካታ ስራዎችን እየሰራን ነው።

ከማገበያየት ጀምሮ ማከማቸት፤ የምርት ደረጃ ሰርተፍኬት መስጠት እና ምርቶችን የማከም አገልግሎት ከግዜ ወደ ግዜ እየተሻሻሉ የመጡ አገልግሎቶች ናቸው። ከትላንት ዛሬ የተሻለ ነው። ከዛሬም ነገ የተሻለ ይሆናል። በተለይ የዲጂታላይዜሽን ስራው ትልቅ አቅም ይሰጠናል። ወደ ኦንላይን ስንሄድ፤ ወደ ቴሌ ክላውድ ሲስተም ስንገባ መጋዘኖቻችን አካባቢ የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ስንተክል ከዛሬ የተሻለ አገልግሎት እንሰጣለን።

**አዲስ ዘመን፡- ሲሚንቶ፤ ስኳር እና የኢንዱስትሪ ጨው ግብይት በምርት ገበያው እንዲካሄድ ለማድረግ ጥናት እየተደረገ እንዳለ በሚዲያ ተነግሮ ነበር። ጥናቱ ምን ደረጃ ላይ ነው? ወደ ትግበራ የሚገባው መቼ ነው?**

**አቶ በኃይሉ፡-** በዚህ ቀን ማለት አንችልም፤ ምክንያቱም ቀኑ በእኛ የሚወሰን አይደለም። እነዚህ ጉዳዮች ረጅም ግዜ ይወስዳሉ። አንዳንዶቹ ጥናቶች ተጠንተው ለረጅም ግዜ ይቀመጡና የሆነ ግዜ ላይ ይነሳሉ። ለምሳሌ ስሚንቶ ላይ ሰፊ የአዋጭነት ጥናት አጥንተናል። የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማየት ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር ንግግር አድርገናል። እንደ ምርት ገበያ ማቅረብ የምንችለው ‹‹ፕሮፖዛል››ነው። ማዕድን ሚኒስቴርም ጥናቱን አይቶ ገምግሞታል። ነገር ግን ያለው ችግር አንድ ምርት ወደ ምርት ገበያ እንዲገባ በበቂ ሁኔታ መመረት መቻል አለበት። ስለዚህ ስሚንቶ ላይ ያለው አንዱ ፈተና በበቂ አለመመረቱ ነው።

አሁን ተስፋ የምናደርገው አዲስ የተገነቡ የስሚንቶ ፋብሪካዎች አሉ። የሀገራችንን የስሚንቶ ምርትን በ50 በመቶ ሊጨምር የሚችል ፋብሪካ አሁን በቅርቡ ተመርቋል። ይህ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ ገበያው ላይ በበቂ ሲሚንቶ እንዲኖር ያስችላል። ከሀገራችን አልፈንም ለኤክስፖርት ልናቀርብ እንችላለን። ያንጊዜ የተደራጀ ገበያ ያስፈልጋል። አሁን ላይ ግን እጥረቱ ስላለ ግብይት የሚፈጸመው ፋብሪካው በር ላይ ነው። በተመሳሳይም የስኳር ምርታማነታችን ላይ እየተሰራበት ነው። ምርቶቹ ገበያ ላይ በበቂ ሲኖሩ የተደራጀ፤ ዘመናዊ፤ ፍትሃዊ እና ተወዳዳሪ ገበያ ስለሚያፈልግ ጥናቱን አጥንተን ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- የጥራት መመርመሪያ መሳሪያዎቹ ምን ያህል ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ እና አስተማማኝ ናቸው?**

**አቶ በኃይሉ፡-** የጥራት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎቻችን ዘመናዊ የሚባሉ ናቸው። ለምዘና ስራ የሚውሉ መሳሪዎች እና የምርት ጥራት መመርመሪያ መሳሪያዎቻችን በየዓመቱ በኢትዮጵያ ስነልክ ኢንስቲትዩት ፍተሻ ይደረግባቸዋል። የስነልክ ኢንስቲትዩት ልኬት ያላደረገባቸው የሚዛን መሳሪዎች፤ የምርት ልኬት መሳሪያዎች እና የምርት ጥራት መሳሪያዎች ስራ ላይ አይውሉም። እንደ ምርት ገበያ በየዓመቱ በዝግጅት ምዕራፍ ከምንሰራቸው ስራዎች አንዱ ያንን መሳሪያዎች ቆጥሮ ለቅሞ ለስነልክ ኢንስቲትዩት የፍተሻ እና የማረጋገጫ ስራ ይሰራልን ብሎ ማቅረብ ነው። መሳሪዎቹ ተፈትሸው ልክ ናቸው ሲባሉ ብቻ ወደ ስራ እናስገባለን።

**አዲስ ዘመን፡- የምትፈልጓቸውን አይነት የጥራት ልኬት ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በበቂ ገበያው ላይ የማግኘት ሂደት ምን ይመስላል?**

**አቶ በኃይሉ፡-** ምርት ገበያው ለራሱ ሲቀጥር አሰልጥኖ እና ፈትኖ ስለሚቀጥር ብዙ ችግር የለም። ብዙ የተማረ የሰው ኃይል ስላለ የራሳችንን አቅም እያሳደግን እና እያሰለጠንን እንሄዳለን። የምርት ገበያ አካዳሚ አንዱ እና ዋነኛው ጠቀሜታው በቡና እና በቅባት እህሎች ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል መፈጠር ነው። ምርቶቻችን በጥራት እንዲመረቱ እና በጥራት ከሀገር እንዲወጡ ከተፈለገ ሰዎች ላይ መስራት አለበት። እውቀት እና ክህሎት ያለው ባለሙያም ያስፈልጋል።

አካዳሚው የሚያደርገውም ተምረው እውቀት ይዘው ቀጥታ ኢንዱስትሪው ላይ የሚሰሩ ሰዎችን ከማፍራት አኳያ በቡና ቅምሻ እና በጥራጥሬና በቅባት እህሎች ስልጠና እየሰጠ ነው። እኛ ስልጠናዎችን እንሰጣለን ለራሳችን ሰዎችን ስንፈልግ አወዳድረን እንቀጥራለን። ኢንዱስትሪዎችም በተመሳሳይ ሰልጣኞችን ይቀጥራሉ። ስለዚህ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያለውንም ክፍተት እንሞላለን።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም ያቀደው እቅድ ምንድን ነው?**

**አቶ በኃይሉ፡-** የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ዘመናዊ በሆነ የግብይት ስርዓት ውስጥ እንዲገበያዩ እናልማለን። ኢትዮጵያ በቅርቡ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ትሆናለች። በአፍሪካ ደረጃ የነጻ ገበያ ስራዎች ተጀምረዋል። እንደምርት ገበያ የአፍሪካ የምርት ገበያ አባል ነን። በዛም የምንሰራቸው ስራዎች አሉ። ራዕያችን በአፍሪካ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ የሆነ የግብይት ማዕከል መሆን ነው። የንግድ ዘርፉ ተዋንያን ፍትሃዊ እና ተወዳዳሪ የሆነ የገበያ ስርዓት ውስጥ እንዲሳተፉ እና በዘመናዊ የገበያ ስርዓት ውስጥ የሚመነጩ መረጃዎችን ለታክስ ስርዓታችን አስተሳስረን በመጠቀም የበለጸገ ሀገር እንዲኖረን ያስችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን!**

**አቶ በኃይሉ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ከረሃብ ነፃ ዓለምን በመፍጠር - የኢትዮጵያ ሚና

**በአዲሱ ገረመው እና ሞገስ ፀጋዬ**

የአፍሪካ ኅብረት ሊቀ መንበር ሙሳ ፋኪ ማህመት፤ የ2025 የአፍሪካ የግብርና ልማት ፕሮግራም ረሃብን ለማጥፋት ብርቱ የሆነ ዓላማን ያነገበ ቢሆንም አፍሪካ ግን ከእቅዱ አኳያ ብዙ የሚቀራት ጉዳይ እንዳለ ያመላክታሉ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያንም ሆነ ለተቀሩት የዓለም ሀገራት ምሳሌ ሊሆን የሚችል የግብርና ልማት ማሳየቷን ይገልጻሉ።

አፍሪካ 60 በመቶ የሚሆን የዓለም ምርታማ መሬት ይዛ መራብ እንደሌለባት የሚገልጹት ሊቀመንበሩ፤ ሆኖም በአሁኑ ወቅት 230 ሚሊዮን አፍሪካውያን የምግብ ዋስትናቸውን አለማረጋገጣቸውን ይጠቁማሉ። በአፍሪካ ኅብረት የተዘጋጀው የተቀናጀ የግብርና ልማት ፕሮግራም በሚፈለገው ልክ ለውጥ አለማምጣቱን አንስተው፤ ይህ ለአሕጉሪቱ አስጨናቂ ጉዳይ እንደሆነ ነው የሚናገሩት።

በዚህ ረገድ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የልማት አጋሮችን እና ሌሎች ቁልፍ ባለ ድርሻ አካላትን ማሳተፍ እንደሚገባ፤ የቴክኒክና የገንዘብ ሀብት እንደሚያስፈልግ ተናግረው፤ ለዚህ ደግሞ ስትራቴጂያዊ እና የድርጊት መርሐ ግብር በመተግበር የምግብ ሥርዓት ለውጥ ማምጣት ለነገ የሚባል ጉዳይ እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ።

የአፍሪካን የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ጥራት ያለው የግብርና ሥራ በመተግበር ምርታማነትን ማስፋፋት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ በተለይም ኢትዮጵያ እየተገበረች ላለው ሞዴል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ሥራዎችም ለሁሉም ተሞክሮ እንደሚሆን አስታውቀዋል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከረሃብ ነፃ ዓለምን ለመፍጠር የበኩሏን ሚና እየተወጣች ትገኛለች። ለአብነትም ባለፉት ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ችላለች። ባለፉት 50 ዓመታት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ታስገባ የነበረውን የስንዴ ምርት ከማስቀረት አልፋ፤ ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች።

ኢትዮጵያ በ2016 በጀት ዓመት ብቻ ከ230 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ማምረት ችላለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ባለፉት ዓመታት 40 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ለግብርናው ዓለም አቀፍ ፈተና የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በመከላከል በግብርናው ላይ ምርታማነትን ማሳደግ ችላለች ሲሉ ገልጸዋል።

ረሃብን ለመከላከል በርካታ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች መኖራቸው የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ በዋናነት የምርጥ ዘር አቅርቦት አለመኖር፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ ግጭት የመሬት መንሸራተት፣ ድርቅ፣ የጎርፍ አደጋ፣ የአንበጣ ወረርሽኝ፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት አለመኖር ዋና ዋናዎች መሆናቸውን አንስተዋል።

ይህም ከረሀብ ነፃ ዓለምን ለመፍጠር የሚደረገውን ትግል አክብዶት እንደነበር ጠቅሰው፤ ይሁንና ኢትዮጵያ ችግሮችን ተከላክሎ ረሃብን ማስወገድ የሚያስችል አቅም መፍጠር መቻሏን አብራርተዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በግብርና ምርታማነት ላይ ስትራቴጂካዊ ለውጥ በማምጣት ሰፋፊ ድሎችን ያስመዘገበች ሲሆን፤ በተለይም የሚታረስ መሬትን በእጥፍ በመጨመር ምርታማነትን ማሻሻል ከተገኙ ውጤቶች አንዱ ነው ብለዋል። ይህም በስንዴ፣ በጤፍ፣ በቆሎ እና ገብስ ምርቶች ላይ ተጨባጭ ለውጥ አምጥቷል ሲሉ አስረድተዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር 40 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸው የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከት እንደቻለ ተናግረዋል።

የተመድ የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (ዩኒዶ) ዳይሬክተር ጄኔራል ገርድ ሙለር እንደሚሉት፤ ረሃብ የዓለም የጋራ ችግር ነው። ይሁንና የጋራ እውቀትን፣ ልምድንና፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በመጠቀም ከረሃብ ነፃ ዓለምን መፍጠር ይቻላል።

አፍሪካ የዓለማችን ባለፀጋ አሕጉር ናት፤ ይሁንና በአሕጉሩ የሚስተዋሉ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ከረሃብ ነፃ ዓለምን ለመፍጠር ትልቅ ፈተና ደቅነዋል ሲሉ ያብራራሉ። ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት በምግብ ምርታማነት ላይ ያስመዘገበችው ስኬት ከረሃብ ነፃ አሕጉር መፍጠር እንደሚቻል ከአፍሪካ አልፎ ለዓለም ሀገራት ትምህርት የሚሰጥ ነውም ብለዋል።

አፍሪካ የተፈጥሮ ሀብት ብዙኃነት ያለባት አሕጉር ብትሆንም አሁንም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አልቻለችም ያሉት ሙሳ ፋኪ በበኩላቸው፤ ረሃብን ከአፍሪካ የማጥፋት ጉዳይም በሁሉም ዘንድ ትኩረት የሚሠጠው መሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም ኢትዮጵያ የወሰደቻውን ርምጃ በማድነቅ፤ ሀገሪቷ እየሳየች ያለው ዓለም አቀፍ ተልዕኮን የመወጣት ብቃት አስመልክቶ የገርድ ሙለርን ተመሳሳይ ሀሳብ ተጋርተዋል።

በአፍሪካ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚቀመጡ የውሳኔ ሀሳቦችን በቁርጠኝነት የመተግበር ክፍተት መሆኑን በመግለጽ፤ አፍሪካን ከረሃብ ነፃ ለማድረግ የሚቀመጡ ውሳኔዎችን ሀገራት በቁርጠኝነት ሊተገብሩት እንደሚገባም ነው ያስገነዘቡት።

ረሃብን ከአፍሪካ ምድር ማጥፋት የአሕጉሪቱ የምንግዜም ስትራቴጂክ ዕቅድ እንደሆነ በማንሳት፣ ይህንን ዓላማ ማሳካትና በአዲስ መንፈስ መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ ሚና መሆኑን ይናገራሉ።

በቀጣይ አካታች በሆነ መንገድ ሥራ ፈጠራን ማበረታታት፤ የንግድ እሴት ሠንሠለትን መፍጠር፤ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ፤ ቀጣይነት ያለው ምርታማነትን መጨመር፣ ግብርናን በፋይናንስ መደገፍ፣ የምግብ ሥርዓት አስተዳደርን ማጠናከርና ሌሎችም መሰል ዒላማዎች ከረሃብ ነፃ ዓለምን ለመፍጠር ትልቅ ድርሻ ያላቸው መሆቸውን ሊቀመንበሩ አንስተዋል።

አፍሪካ በተፈጥሮ ሃብቶች የበለፀገች በመሆኗ ያላትን እምቅ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ትችላለች ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከረሃብ ነፃ ዓለም ለመፍጠር በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዘዴዎችን መከተል እንደሚገባ ይመክራሉ። በተለይ ዘመናዊ የግብርና ግብዓቶችን መጠቀም፣ የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ፣ ድርቅን የሚከላከሉ ሰብሎችን መዝራት፣ ግጭትን ማስቆምና መሠረተ ልማትን ማስፋፋት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች መሆን እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ምግብ ወደ ሀገር ከማስገባት ወደ ውጭ ወደ መላክ ተሸጋግራለች። ይህ በሁሉም አፍሪካ ሀገር እውን መሆን ይችላል። “ለዚህ ኢትዮጵያ ማሳያዋ ናት” በማለትም ኢትዮጵያ በምግብ ምርታማነት ላይ ላስመዘገበችው ለውጥ አድናቆታቸውን ይገልጻሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ አፍሪካ ካላት የተፈጥሮ ሀብት አንጻር ረሃብን ማስቆም ትችላለች። አፍሪካ ለግብርና የሚውል ሰፊ የሚታረስ መሬት አላት። በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ከድህነት ወደ እድገት ጎዳና እየመጡ ነው፣ የኢትዮጵያም አንዷ ማሳያ ናት።

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ ከረሃብ ነፃ ዓለምን ለመፍጠር በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ብቻ 50 ቢሊዮን ዶላር ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልጋል።

# ኢትዮጵያ ረሃብን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምርታማነትን ከማሻሻል በላይ በግብርና ዘርፍ ላይ የሚታዩ መዋቅራዊ ችግሮች መፍታት ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚታረስ መሬትን በእጥፍ በመጨመር ምርታማነትን ማሻሻል መቻሉንም ጠቅሰው፤ በስንዴ፣ በጤፍ፣ በቆሎና ገብስ ምርቶች ላይ ተጨባጭ ለውጥ መመዝገቡን አንስተዋል።

በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት 230 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በማምረት የሀገር ውስጥ ፍጆታን በመሸፈን ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሉን ተናግረዋል። በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አማካኝነትም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ መገንባት መቻሉን ገልጸዋል።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ካደረገችባቸው ዘርፎች መካከል የግብርናው ዘርፍ ተጠቃሽ መሆኑን ጠቁመው፣ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል በግብርናው ዘርፍ ባከናወነችው ዘርፈ ብዙ ተግባራት በተባበሩት መንግሥታት የምግብ እና እርሻ ድርጅት (ፋኦ) መሸለሟንም አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ባለፉት ዓመታት ግብርናን ከኢንዱስትሪ ጋር በማስተሳሰር ትልቅ ለውጥ ማምጣቷን የገለጹት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማስፋፋት፣ የግል ዘርፉን በማበረታታት ኢትዮጵያ በዘርፉ ውጤታማ ለውጥ እንድታመጣና ዓለም አቀፍ እውቅናን እንድታገኝ ያስቻሏት ጥረቶች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት(ዩኒዶ)፣ የአፍሪካ ኅብረት፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም የምግብ ድርጅት (ፋኦ) በጋራ ያዘጋጁት ከረሃብ ነፃ ዓለም ጉባኤ ከትናንትና ጀምሮ ለቀጣይ ሦስት ቀናት በአዲስ አበባ እየተካሄደ ይገኛል። በጉባኤው ከአንድ ሺህ 500 በላይ ባለድርሻ አካላት እየተሳተፉ ነው። በዋናነት ዓለማችን የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ችግርን ከመሠረቱ ሊፈቱ የሚችሉ የመፍትሔ ሐሳቦች ላይ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የሚመከር ጉባኤ መሆኑን ተገልጿል።

# ኢትዮጵያን የዓለም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የማስተናገድ አቅም ያለው አዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ልማትን ጨምሮ በርካታ መሠረተ ልማቶች ላይ ኢንቨስት እየተደረገ መሆኑን አስታውሰዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው በበኩላቸው፤ አየር መንገዱ የተረከበው አውሮፕላን ከኤርባስ ኩባንያ የተገዛ ነው። አየር መንገዱ ካዘዛቸው አራት አውሮፕላኖች መካከል አንዱ መግባቱን ገልጸው፤ ቀሪዎቹ በየወሩ እንደሚመጡ አስታውቀዋል።

ኤ350-1000 አውሮፕላን ነዳጅ ቆጣቢ መሆኑ፣ የኤሌክትሪክ ሥርዓቱ፣ ባሉት የመቀመጫ ወንበር ብዛት፣ በመንገደኞች መገልገያ ቁሳቁሶች፣ በመንገደኞች የመዝናኛ አማራጮች እጅግ ዘመናዊና ያደርገዋል ብለዋል።

የአውሮፕላኑ ወደ ገበያ መግባት የአየር መንገዱን የመሪነት ሚና ለማስቀጠል እንዲሁም ስምና ዝናውን ይበልጥ ለማጉላት እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመዳረሻ እና በአውሮፕላን ብዛት፣ አዳዲስ አውሮፕላኖችን በማስመጣት ከአፍሪካ አየር መንገዶች መንገደኞች ቀዳሚ መሆኑን ተናግረዋል።

አየር መንገዱ የመሪነት ሚናውን ለማስቀጠልና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከ120 በላይ አውሮፕላኖችን ለማስመጣት መታዘዙን እና በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደሀገር ውስጥ እንደሚገቡ አመላክተዋል።

በተጨማሪም አዳዲስ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች ለማስፋፋት እየተሠራ ሲሆን፤ ይህም የመንገደኞችን ቁጥር እና ገቢው እንዲያድግ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል።

# አሳሳቢው የሱስ ተጠቂነት እና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሱሰኝነት አንድን ወይም የተለያዩ ሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮችን (ትምባሆ፣ መጠጥ፣ አበረታች መድኃኒት እና ጫት) በተደጋጋሚ መጠቀምና የንጥረ ነገሮቹ ጥገኛ የመሆን ችግር ነው። እነዚህን ንጥረ ነገሮች አንድ ሰው በገዛ ፈቃዱ ቢጀምራቸውም በጊዜ ሂደት ግን አዕምሮውን፣ ጊዜውን አካሉን የሚቆጣጠሩ የራሳቸው ጥገኛ የማድረግ ባሕርይ ስላላቸው ለማንኛውም በሱስ ለተጠቃ ሰው እንደ ጅማሮው ቀላል አይሆንለትም። ሱሰኝነት የአዕምሮ ጤናን የሚያውክ ማኅበራዊ ቀውስንም የሚስከትል ሲሆን ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሱስ ሊገቡ ይችላሉ። ስለሱስ ተያያዥ መዘዞቹና መፍትሔዎቹ ያነጋገርናቸው የዘርፉን ባለሙያዎችም በጉዳዩ ዙሪያ አመክንዮታዊ ሃሳባቸውን አቅርበውልናል።

ሲስተር ይርገዱ ሀብቱ አዲስ ሕይወት የተሰኘ የዕፅና አልኮል ሱሰኝነት ሕክምናና ማገገሚያ ማዕከል መሥራች ናቸው። ለሱስ አጋላጭ ምክንያቶች በርካታ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ 10 ሰዎች ወደ ሱስ የገቡበትን ምክንያት ቢጠየቁ 10 ዓይነት ምክንያት ሊናገሩ ይችላሉ። በተለይ በአቻ ግፊት፣ በግንዛቤ ችግር፣ መዝናናት በሚል ሰበብ፣ ለጥናት ይጠቅማል በሚል፣ ከአቅም በላይ ሠርቶ ገንዘብ በማግኘት፣ ሥራ በማጣት፣ ገንዘብ በማጣት፣ በትዳር እና በቤተሰብ መካከል በሚፈጠር ችግር፣ በቤተሰብ መካከል ሱስ አምጪ ንጥረ ነገር ተጠቃሚ በመኖሩ፣ በሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ወይም ፈተናዎችን ለመሸሽ ወይም ጊዜያዊ ችግሮችን ለመርሳት የሚሉና እና ሌሎችም ወደ ሱስ ከገቡ ሰዎች ከሚደመጡ ምክንያቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በአቻ ግፊት ወደ ሱስ ሕይወት እንደገባ ያጫወተን የ29 ዓመቱ ወጣት ተካልኝ ከበበው፤ መጀመሪያ ሲጋራ ያጨሰው በ16 ዓመቱ እንደነበር ያስታውሳል። በዚያን ወቅት በዕድሜ ያልበሰለበት፣ ሲጋራ ማጨስ እንደ አራዳነት የሚቆጠርበት



ጊዜ እንደነበር ይናገራል። “እንደ ቀልድ ከጓደኞቼ ጋር እየተቀባበልኩ የጀመርኩት ሲጋራ ወደ ጫትና አልኮል ተጠቃሚነት ተሻግሮ ሕይወቴን አበላሽቶብኛል” ይላል።

ወጣቱ እንደነገረን ቤተሰቦቹ ጥሩ ገቢ ያላቸው የሚያስፈልገውን ብቻ ሳይሆን የሚጠይቀውን ሁሉ የሚያደርጉለት ነበሩ። የእርሱ ወደ ሱስ መግባትና ከቤተሰቡ ትዕዛዝ መውጣት በወላጆቹ መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር እንዳደረገም ያስታውሳል። በእናትና በአባቱ መካከል ለእሱ መበላሸት አንዳቸው አንዳቸውን ሲከሱ የሚፈጠረው ጭቅጭቅና ሠላም ማጣት በጊዜው ለእርሱ ምንም ትርጉም ይሰጠው እንዳልነበረም ይጠቁማል።

ከሱስ ሕይወት ለመውጣት ፍላጎት ቢኖረውም፣ ከሱስ ጥገኝነት መላቀቅ ባለመቻሉ በመኖሪያ አካባቢው በሚገኝ ኤምባሲ ፊት ለፊት ጉዳይ ለማስፈፀም የሚመጡ ሰዎችን መኪና በመጠበቅና መረጃ በመስጠት በሚያገኘው ሳንቲም እና ቤተሰቦቹ በሚሰጡት ገንዘብ በመያዝ የሱስ ፍላጎቱን ያሟላል።

በእኔ ተስፋ ያልቆረጠችው እናቴ ብቻ ናት ያለው ወጣት ተካልኝ፤ አባቱ እነርሱንም ያበላሻል በሚል ከታናናሽ ሁለት ወንድሞቹ ጋር እንኳ እንዲቀራረብ እንደማይፈልግ በኃዘን ስሜት ይናገራል። ምግብ ላይ ብዙም አይደለሁም ያለው ወጣቱ በተለይ ሳንባው ክፉኛ እንደተጎዳና ሲጋራ ማጨሱን የማያቆም ከሆነ ለከፋ ችግር እንደሚያጋልጠው በሐኪም እንደተነገረው ይገልጻል።

ሲስተር ይርገዱ በበኩላቸው፤ የሱስ ጥገኛ የሆኑ ሰዎች፤ ምንም ያህል ገንዘብና ጥሩ ገቢ ቢኖራቸው ገንዘብ መያዝ ካለመቻላቸውም ባለፈ ያላቸውንም እያጡ እንደሚሄዱ ይናገራሉ። እንዲህ አይነት ኑሮን ያሳለፉ ከሱስ የተነሳ ከቤተሰቦቻቸው የተጋጩና የተለያዩ፣ ትዳራቸው የተበተነ፣ ትምህርትና ሥራቸውን ያጡ፣ ኢኮኖሚያቸው የተጎዱ በርካታ የሱስ ተጠቂዎች መኖራቸውንም ያነሳሉ።

ሱስ የራስ ሕይወትን ከማቃወስ ጀምሮ ቤተሰብን የሚያወክ፣ ማኅበራዊ ተቀባይነትንም የሚያሳጣ እንደሆነ የሚናገሩት ሲስተር ይርገዱ፤ ማኅበረሰቡ ሱስ ታክሞ መዳን የሚችል በሽታ መሆኑን ባለመረዳቱ በሱስ የተጠቁ ሰዎችን ዝቅ አድርጎ የማየት፤ የማይረቡ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ እንዳለ ያስረዳሉ። ይህ አይነቱ የማኅበረሰቡ ዕይታ በሱስ የተጠቁ ሰዎችም ራሳቸውን የማይረቡ አድርገው እንዲቆጥሩ እንደሚያደርጋቸውም ያስረዳሉ።

ሱሰኝነት በግለሰቡ ላይ ከሚያስከትለው የጤና ችግርና ማኅበራዊ ቀውስ ባለፈ በሀገር ላይም አሉታዊ ውጤትን የሚያስከትል ነው ያሉት ሲስተር ይርገዱ፤ በሀገራችን እየጨመረ የመጣው የትራፊክ አደጋና ልዩ ልዩ አይነት ወንጀሎች በአብዛኛው ከሱስ ሕይወት ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው ይጠቅሳሉ።

ማዕከላቸው ከሱስ ሕይወት ማላቀቅ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን የተናገሩት ሲስተር ይርገዱ፣ ቅድመ መከላከል ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት ይገባል ይላሉ። አንድ ሰው ወደ ሱስ ጥገኝነት እየተጓዘ መሆኑን ከተረዳን፣ ይህ ሰው ጤናው ከመታወኩ፣ ስርቆት ውስጥ ከመግባቱ፣ ጎዳና ላይ ከመውጣቱ፣ ሌሎችንም ችግሮች ከመፈጠራቸው አስቀድሞ ርዳታ ወደሚያገኝበት የማገገሚያ ማዕከላት መውሰድ እንደሚገባም ያሳስባሉ። ግለሰቡ ለመለወጥ ከቆረጠ ከሱስ መላቀቅ ይቻላል ያሉት ሲስተር ይርገዱ፣ ሱሰኝነት ታክሞ መዳን የሚችል በሽታ ነው የሚለው ላይ አፅንዖት ሰጥተዋል።

# ንግድና ግብይት

# የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይትን ለውጭ ገበያ ማቅረብ የጀመረው አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሥራዎች መካከል የተቀናጁ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማልማት፣ ማስተዳደርና ለአልሚ ባለሃብቶች ማስተላለፍ ነው:: የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ በዋናነት በእሴት ጭመራ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን፤ ይህም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር፣ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርና የግብርና ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ማስቻል፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ የሚያግዝ ነው::

በአገሪቱ ከሚገኙ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል ወደ ሥራ የገባው ዲላ መካከለኛ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ አንዱ ሲሆን፤ ፓርኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመረተውን ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት ለውጭ ገበያ ማቅረብ ችሏል::

የደቡብ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን ብርሃኑ በተለይ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ የዲላ መካከለኛ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ለመጀመሪያ ጊዜ ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት ኤክስፖርት ማድረግ መቻሉን ይፋ አድርገዋል::

ፓርኩ በቅርቡ 22 ቶን የሚጠጋ ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት ለመጀመሪያ ጊዜ ለውጭ ገበያ ማቅረብ መጀመሩን የገለጹት አቶ ጥላሁን፤ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የአቦካዶ ድፍድፍ ዘይት እያመረተ ያለውም «ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ» የተባለ አገር በቀል ድርጅት እንደሆነ ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ «ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ ማህበር በአንድ ፈረቃ 22 ቶን የሚጠጋ ድፍድፍ የአቦካዶ ዘይት አምርቶ ወደ ጣሊያን አገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ጀምሯል:: ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይቱ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ሲሆን፤ አሁን ወደ ጣሊያን የተላከው ለኮስሞቲክስ ግብዓት የሚውል ነው:: የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይቱ ተጣርቶ ለተለያዩ የኮስሞቲክስ አገልግሎቶችና ለሌሎች ምርቶችም በግብዓትነት እንዲያገለግል ይደረጋል::

በዲላ አካባቢ አቮካዶ በስፋት የሚመረት እንደመሆኑ ይህን መሰረት በማድረግ ወደ ምርት የገባው ኢትዮጵያዊው ባለሃብት፣ ወደ ማምረቱ የገባውም ባለፈው ዓመት ነው:: በጌዲዮ ዞን ዲላ አካባቢ በዓመት ሁለት ጊዜ የአቮካዶ ምርት የሚሰበሰብ በመሆኑ ድርጅቱ የደረሰውን የአቮካዶ ምርት በመጠቀም በአሁኑ ወቅት 22 ቶን ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት አምርቶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጀምሯል:: ድርጅቱ በሶስት ፈረቃ የማምረት አቅም ያለው ሲሆን፣ አሁን በአንድ ፈረቃ ብቻ በማምረት ምርቱን ወደ ጣሊያን ልኳል::

ምርቱን ወደ ሌሎች አገራት ለመላክ አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ወደ አሜሪካና ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ገበያ ለመግባትም ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል:: ምርቱ ኦርጋኒክ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ከኮስሞቲክስ አገልግሎት ባለፈ ለምግብነት እንዲውል የሚደረግ መሆኑንም ተናግረዋል:: አገልግሎቱን የገበያ መዳረሻውን ለማስፋት የክልሉ መንግሥት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እየሰራ መሆኑንም ገልጸዋል::

አሁን የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይቱን በአንድ ፈረቃ ብቻ እያመረተ ያለው ይህ ድርጅት 60 ለሚደርሱ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠሩንም ጠቅሰዋል:: በቀጣይ በሶስት ፈረቃ ማምረት ሲጀምር ደግሞ 160 ለሚደርሱ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ይሆናል ሲሉም አስታውቀው፣ ድርጅቱ በቀጥታ ከፈጠረው የሥራ ዕድል በተጨማሪ ሶስት ሺ ከሚደርሱ አቮካዶ አምራች የአካባቢው አርሶ አደሮች ትስስር በመፍጠር የአቦካዶ ምርት በወቅቱ እየተረከባቸው መሆኑን ገልጸዋል::

ከ17 እስከ 20 የሚደርሱ የሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖችም ከድርጅቱ ጋር የገበያ ትስስር መፍጠራቸውን ተናግረዋል:: በዚህም በጌዲኦ ዞንና እና በሲዳማ ክልል የሚገኙ አቡካዶ አምራች ዩኒየኖች በተፈጠረላቸው የገበያ ትስስር መሰረት የአቮካዶ ምርት ለኢንዱስትሪው እያቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል:: በዚህም በቀጥታና በተዘዋዋሪ ሰፊ የሥራ ዕድል መፈጠሩን አስታውቀዋል::

**ፓርኩ በቅርቡ 22 ቶን የሚጠጋ ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት ለመጀመሪያ ጊዜ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጀምሯል፤ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የአቦካዶ ድፍድፍ ዘይት እያመረተ ያለውም ‹‹ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ›› የተባለ አገር በቀል ድርጅት ነው**

አቶ ጥላሁን እንዳብራሩት፤ በጌዲኦ ዞን የአቮካዶ ምርት በበቂ ሁኔታ አለ:: በተመሳሳይ በደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታ ዞን ላይም አቮካዶ በስፋት ይመረታል:: አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ከሚገኝበት ዲላ ከተማ ከ100 እስከ 150 ኪሎ ሜትር ባለ ርቀት የሚገኝ ሲሆን፣ የአቮካዶ ምርቱን የትራንስፖርት ችግር የሌለ በመሆኑ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል::

በአሁኑ ወቅት ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጌዲዮ ዞን አካባቢ እንዲሁም ሲዳማ ክልል ላይ የተወሰነ የአቮካዶ ምርት እየገባ ይገኛል:: በቀጣይም ድርጅቱ የማምረት አቅሙን እያሳደገ ሲሄድ በደቡብ ኢትዮጵያ ወላይታና አቮካዶ በከፍተኛ መጠን በሚመረትበት ጌዲዮ ዞን ያለውን ሰፊ የአቮካዶ ምርት በመቀበል የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይት በከፍተኛ መጠን ማምረት ይቻላል::

በዚህም ለአካባቢው ወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይደረጋል፤ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለአገሪቷ በማስገኘት በኩልም ትልቅ አበርክቶ ያደርጋል:: በተለይም ምርትና ምርታማነት እንዲጨምርና አቦካዶን በተለየ መንገድ ለማልማት ያግዛል::

ጥሩ የዘይት አቅም ያላቸውን የአቮካዶ ዝርያዎችን ችግኝ በማፍላት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ትልቅ ሥራ እየተሰራ ሲሆን፤ አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ሕብረት ሥራ ማህበራት የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ ነው::

በተለይም ቴክኖሎጂ መጠቀም እንዲቻልና ተጨማሪ የዘርያ ማሻሻያ ማድረግ እንዲቻል የልማት አጋር ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታትና የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት በስልጠናና በተለያየ መንገድ ድጋፍ እያደረጉ ነው:: ፓርኩ በተለይም ጂ አይ ዜድ ከተባለ አጋር የልማት ድርጅት ጋር በተለይም አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂውን በሰፊው መጠቀም እንዲችል፣ ዝርያውን አሻሽሎ የተሻለ ምርት እንዲያመርትና እንዲያሳድግ በዚህም ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በጋራ እየሰራ ይገኛል::

ፓርኩ በቅርቡ ወደ ሥራ የሚገቡ የተለያዩ ምርቶች እንዳሉትም ዋና ስራ አስፈጻሚ ገልጸው፣ በአሁኑ ወቅት ፍላጎት ያሳዩ አስር የሚደርሱ የአገር ውስጥና የውጭ ባላሃብቶች እንዳሉ ጠቁመዋል:: አሁን የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይት ማምረት የጀመረው «ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ» ማህበር በቡና ልማት ጭምር የተሰማራ ባለሃብት በመሆኑ በቀጣይ ቡና ላይ እሴት በመጨመር ቆልቶ፣ ፈጭቶና አሽጎ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል:: ሌሎች በኢንዱስትሪ ፓርኩ ለመሥራት ፍላጎት ያሳዩ ባለሃብቶች እንዳሉ አመላክተዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኩ መሰማራት በሚያስችሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ ሰፋፊ ጥናቶች ተደርገዋል:: አሁን መካከለኛ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ እየተሰራ ሲሆን፣ የዲላው የኢንዱስትሪ ፓርክ በአስር ሄክታር መሬት ላይ የተገነባ ነው:: ግንባታውም ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ወደ ስራ ገብቷል::

የግንባታው 95 በመቶ የተጠናቀቀው የይርጋጨፌ ኢንዱስትሪ ፓርክ በክልሉ ሁለተኛው መካከለኛ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ከስድስት ወራት በኋላ ሙሉ ለሙሉ ግንባታው ተጠናቅቆ ወደ ሥራ እንደሚገባም ጠቁመዋል:: በቡና ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች በይርጋጨፌው አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ቡና ላይ እሴት ጨምረው ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጁ መሆናቸውንም አስታውቀዋል::

ዋና ስራ አስፈጻሚው እንዳብራሩት፤ የይርጋጨፌ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ እስከ አስር የሚደርሱ ባለሃብቶችን የመቀበል አቅም አለው:: በመሆኑ ከቡና በተጨማሪም ወተት፣ ማርና ሌሎች ፍራፍሬዎች ማቀነባበር ላይ የመሰማራት ፍላጎት ያላቸው የአገር ውስጥ አልሚ ባለሃብቶች ማልማት የሚችሉበት ሁኔታም ተመቻችቷል::

በአካባቢው በሚገኙ የግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ከአርሶ አደሩ ማሳ እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ ያለውን ትስስር ማጠናከር ያስፈልጋል:: በግብርናው ከሚያመጣው የሥራ ዕድል ባሻገር አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሰፊ የሆነ የሥራ ዕድል እንዲፈጠሩ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር፣ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲሰፋና የገበያ ትስሰሩ እንዲጎለበት የማድረግ አቅማቸው ከፍተኛ በመሆኑ ሊሰራበት ይገባል::

ከፍተኛ የገበያ ትስስር ሲፈጠር አርሶ አደሩ በምርቱ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ በአካባቢው የሚመረቱ አቮካዶን ጨምሮ ሌሎች ምርቶችም እሴት ካልተጨመረባቸው ለብክነት ተጋላጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ሰፊ እንደሆነም አመልክተዋል:: በመሆኑም ምርቶቹን በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ፕሮሰስ ማድረግ አዋጭ መሆኑን አስታውቀዋል:: በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በአራትና ከዛ በላይ በሆኑ ክልሎች አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ እየሰራች መሆኗንም ተናግረው፣ ከእነዚህ መካከልም አንዱ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መሆኑንና በቀጣይም ይሄው እየሰፋ እንደሚሄድ ገልጸዋል::

አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለኢትዮጵያ አዲስ መሆናቸውን አቶ ጥላሁን ጠቅሰው፣ ከግብርና ሚኒስቴርና ከሌሎች ተቋማት ጋር ጥብቅ ትስስርና ቅንጅት ማድረግን እንደሚፈልግ ይገልጻሉ:: በተለይም ከጥናትና ምርምር ጋር ተያይዞ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከቴክኒክና ሙያ እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ቢሮና ከስራ ዕድል ፈጠራ ጋር ተቀናጅቶ መስራትን እንደሚጠይቅ አመልክተው፣ ሁሉም አካላት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው ገልጸዋል:: አሁን በቅንጅት ከመስራት አንጻር ያለውን ክፍተት ለመሙላትም በጋራ እየተሰራ እንደሆነም ተናግረዋል::

ከኃይል አቅርቦት ጋር ተያይዞ ክፍተት እንዳለም ጠቁመው፣ የመብራት መቆራረጥ ለስራው እንቅፋት እንደሆነም አስታውቀዋል:: ችግሩን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት እየተደረገ እንደሆነም ይገልጻሉ:: አሁን በአንድ ፈረቃ እየተመረተ ያለው የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይት በቀጣይ በሶስት ፈረቃ ያመርታል ሲባል ያለምንም የኃይል መቆራረጥ ነው ሲሉ አብነት ጠቅሰው ያመለከቱት አቶ ጥላሁን፣ ይህን የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መሰል ችግሮችን ከወዲሁ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል::

ዋና ስራ አስፈጻሚው እንዳስታወቁት፤ የአቮካዶ ድፍድፍ ዘይት እያመረተ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የጀመረው «ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ» ማህበር በቀጣይ በሶስት ፈረቃ ወደማምረቱ ይገባል:: በዚህ ጊዜም አሁን እያመረተ ካመረተው 22 ቶን በላይ በዓመት እስከ 130 ቶን የማምረት አቅምም አለው:: የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪም እንዲሁ ከፍ የሚል ሲሆን፣ አሁን ላይ አንድ ሊትር ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት በአማካይ እስከ 30 ዶላር ገቢ እያስገኘ ነው::

ከጣሊያን ውጭ ያሉ እንደ አሜሪካ፣ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮችና ሌሎች አገራትም ድፍድፍ የአቮካዶ ዘይት የመግዛት ፍላጎት ያሳዩ በመሆናቸው ምርቱን በስፋት ማምረት ይገባል:: ከአቮካዶ በተጨማሪም ሌሎች ሰፊ የገበያ ፍላጎት ያላቸው ምርቶች ስለመኖራቸውና እዛም ላይ መሥራት ያስፈልጋል::

የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም አስመልክቶ ሲያብራሩም አሁን አቮካዶ እየለማ ያለው ሰፊ በሆነ ማሳ ሳይሆን፤ አርሶ አደሩ ባለው የአቮካዶ ዛፍ መጠን ነው ሲሉም ገልጸዋል:: እያንዳንዱ አርሶ አደር አምስትና አስር የአቮካዶ ዛፍ እንዳለው ጠቅሰው፣ እነዚህ አርሶ አደሮች በጋራ ሕብረት ሥራ ማህበር መስርተው ከአልሚ ባለሃብቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የአቮካዶ ምርታቸውን እያቀረቡ እንደሚገኙና ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል::

በእያንዳንዱ አርሶ አደር ማሳ ውስጥ የአቮካዶ ዛፍ እንዳለም አመልክተው፣ ከአቮካዶ ምርት ጋር ተያይዞ የተለያዩ ስልጠናዎች ለአርሶ አደሩ እየተሰጠ መሆኑንም ጠቅሰዋል:: በዚህም የተሻለ ውጤት እየተመዘገበ እንደሆነና የአቦካዶ ድፍድፍ ዘይት ወደ ውጭ ገበያ እየተላከ መሆኑን አስታውቀው፣ ቡና፣ ወተት፣ ማርና በሌሎች ምርቶችም እየተሰራ ያለው ሥራ አበረታችና ውጤታማ መሆኑንም ተናግረዋል:: ምርቶቹ በስፋት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡበት ሂደት ስለመኖሩ ገልጸዋል::

የአካባቢው ከፍተኛ መጠን ያለው የአቮካዶ ምርት እንዳይባክን ፋብሪካ መገንባት ማስፈለጉን አቶ ጥላሁን ተናግረው፣ በአሁኑ ወቅትም የዲላው የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ቴክኖሎጂ በማሸጋገርና በሥራ ዕድል ፈጠራ ካለው አስተዋጽኦ ባለፈ የአቮካዶ ዘይት ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ መጀመሩ ክልሉ በእድገትና ሽግግር ምዕራፍ ላይ እንዲሚገኝ የሚያሳይ ነው ብለዋል። በቀጣይ በፍራፍሬም ሆነ በሌሎች ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ስራ መሰማራት ለሚፈልጉ አልሚ ባለሃብቶች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት እንዲመጡ ዋና ስራ አስፈጻሚው ጥሪ አቅርበዋል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ቅንነት ለጤና

**ዋለልኝ አየለ**

«ፍቅር ወጪ ቆጣቢ ነው» ሲሉ ሰምቼ ነበር መጋቢ ሐዲስ እሸቱ ከዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው አንድ መድረክ ላይ:: «ፍቅር ካለ አንድ እንጀራ ለዘጠኝ ይበቃል» የሚል ሀገርኛ ብሂልም አለ:: የቁጥሩ ብዛትና የምግቡ አይነት ምናልባት ከአካባቢ አካባቢ ይለያይ ይሆናል:: ብቻ ግን ፍቅር ካለ ትንሽ ነገር ያጠግባል::

«ከፍትፍቱ ፊቱ» የሚባለው አባባል ገላጭ የሆነ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው:: አንድ ሰው እየተነጫነጨና እየተቆጣ ብዙ ወይም የቅንጦት የሚባል ውድ ምግብ ከሚሰጠን፤ በፍቅር ቁራሽ ዳቦ ቢሰጠን ታስደስተናለች:: ያቺ ቁራሽ ዳቦ የሕሊና ጥጋብ ታጠግበናለች:: የሰው ልጅ ልባዊ (አሳቢ) ነውና ከሥጋ ጥጋብ ይልቅ የሕሊና ጥጋብ ይበልጥበታል:: በሕሊናው የሚቀረጽ ነገር በመላ ሰውነቱ ላይ ሚና ይኖረዋል::

ለምሳሌ፤ ሰዎች ከባድ ኀዘን ላይ ሲሆኑ ምግብ አይበሉም:: ለምን? ሕሊና ላይ የተፈጠረው የመረበሽ ነገር ሥጋዊ የሆነውን የምግብ ፍላጎት የመቆጣጠር አቅም አለው ማለት ነው:: የትዝብታችን ጭብጥ ስለምግብ ለማውራት አይደለም:: «ከፍትፍቱ ፊቱ» የሚለው ሀገርኛ ብሂል ከሕሊና እና ከቅንነት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሰብ ነው::

የዛሬ ትዝብታችን ቅንነቶቻችንን መታዘብ ነው:: በብዙ ቦታዎች የምናስተውለው ችግር ነው:: ምንም እንኳን ሁላችንም የምናስተውለው ቢሆንም በየአጋጣሚው ትዝ የሚሉኝና የሚገርሙኝን ከዓመታት በፊት ያጋጠሙኝ ሁለት ገጠመኞች መነሻ ላድርግ::

አዋሽ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ውስጥ ነው:: ደንበኞች በተቀበልነው የወረፋ መጠበቂያ ትኬት ቁጥር መሠረት ወረፋችንን እየጠበቅን ነው:: አንድ ደንበኛ፤ ገባና ቅጽ ከሞላ በኋላ ሠራተኛ የሌለበት ባዶ መስኮት ላይ ቆመ:: ከባዶው መስኮት ቀጥሎ ያለው የባንኩ ሠራተኛ (ቴለር) ሰውየውን አናገረው፡ ሰውየውም ወደ ቴለሩ ሄደና የሞላውን ቅጽ ዘረጋ:: የባንክ ቴለሩ ቅጹን ሳይቀበል ሰውየው ወረፋ መያዝ እንዳለበት ነገረው:: ሰውየው (ደንበኛው) «ታዲያ ለምን ጠራኸኝ?» ሲል ደነፋ:: ቴለሩም ደንበኛው የቆመበት መስኮት ለጊዜው ሠራተኛ እንደሌለውና እዚያ መቆሙ ምንም ጥቅም እንደሌለው ነገረው:: ደንበኛው ሊሰማ ነው እንዴ!

ከብዙ ልመና እና ማግባባት በኋላ የባንኩ ሠራተኛ ወጣት ነበርና ትዕግሥቱ አለቀ፤ ወደ መሰዳደብና መዘላለፍ ገቡ:: ሁነቱን ሲታዘቡ የነበሩ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ሰውየውን (ደንበኛውን) ፈረዱበት:: ቴለሩንም አመስግነው «አንተ ዝም ብትል ይሻላል» ብለው ለምነው ዝም አለ:: ሰውየውም የሞላውን ቅጽ እየቀደደና እየተሳደበ ጉዳዩን ሳይፈጽም ሄደ::

ምንም እንኳን ሰዎችን በአለባበስና በአካላዊ ገጽታ ምንነታቸውን ማረጋገጥ ባይቻልም፤ ያ ሲያተራምስ የነበረ ሰውዬ የተማረ የሚባል አይነት አለባበስና አካላዊ ገጽታ ያለው ነው:: ውድ ቦርሳ ያነገተ ነው:: የሥልጡንነት አርዓያ መሆን የሚገባው ነበር::

እዚህ ላይ አንድ ነገር ሊባል ይችላል:: ከሥራ ሥነ ምግባር አንፃር ቴለሩ ታጋሽ መሆን አለበት፤ ግን በታገሰው ቁጥር ሰውየው ጭራሽ እየባሰበት ሄደ:: ስለዚህ ሰውየውን ላለማስከፋት ቴለሩ ምን ማድረግ ነበረበት? ያለወረፋው ማስተናገድ? ይሄ ደግሞ ሌላ የመርሕ ጥሰት ነው::

አንዳንድ እንዲህ አይነት ሰዎች አሉ:: ትሕትና እና ቅንነት የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው ብቻ ሳይሆን፤ ሲደረግላቸውም የማይወዱ፤ በትሕትና እና በቅንነት ባናገሯቸው ቁጥር ጭራሽ የሚብስባቸው አሉ:: «ሞኝ ሲያከብሩት የፈሩት ይመስለዋል» የሚባለው አይነት ማለት ነው::

የዚህን ተመሳሳይ አንድ ልጨምር:: የመንግሥት ሠራተኞች ማመላለሻ የሆነው «ፐብሊክ ሰርቪስ» ውስጥ ያጋጠመኝ ነው:: ሰርቪሱ ለመጫን እና ለማውረድ ሲቆም፤ እንደ በቆሎ እና ቆሎ ያሉ ነገሮችን ይዘው በበር እና በመስኮት በኩል ብቅ የሚሉ ልጆች አሉ:: አሽከርካሪው ማንም የሰርቪሱ ተጠቃሚ እንዲህ አይነት ነገሮችን እንዳይገዛ አስጠንቅቋል መሰለኝ:: እኔም በዚያ ሰርቪስ የሄድኩት የዚያን ቀን ነው::

ላምበረት መናኸሪያ ፊት ለፊት ካለው ፌርማታ እንደቆመ፤ በቆሎ የያዘች ልጅ ወደ ሰርቪሱ በር መጣች:: አንደኛው ተጠቃሚ ሊገዛ ሲል አሽከርካሪው ጮኸበት:: «ይቅርታ!» ብሎ ተወው:: አሽከርካሪው «እንዳትገዙ ብዬ አላስጠነቀቅኩም ነበር ወይ?» ብሎ በቁጣ ጠየቀ:: ተጠቃሚውም ከዚህ በፊት በዚህኛው ሰርቪስ ሄዶ እንደማያውቅና ማስጠንቀቂያውን እንደማያውቅ በትሕትና ተናገረ:: ሌሎች የሰርቪሱ ቋሚ ተጠቃሚዎች «ገና ዛሬ ነው የመጣ» እያሉ ለማግባባት ሞከሩ:: የፐብሊክ ሰርቪስ ተጠቃሚ በአንድ መስመር የሆነ ሁሉ ባገኘው ይሄዳል እንጂ የግድ በአንድ ተሽከርካሪ ብቻ አይሆንም::

አሽከርካሪው አሁንም አምርሮ ይቆጣል:: ያ እንግዳ ተጠቃሚ ሰውየም ያለመታከለት «ይቅርታ!» ይላል:: የአሽከርካሪው ቁጣ ግን እየባሰበት ሄደ:: ይህኔ ተጠቃሚውም ከብዙ ይቅርታ በኋላ «እንዴ! አልገዛሁም እኮ! ‹አይቻልም!› አልከኝ ተውኩት! ለማሰቤም ይቅርታ ጠየቅኩህ!» እያለ ፈርጠም ብሎ ተናገረ:: ይህኔ አሽከርካሪው ቁጣው ጨምሮ «ውረድ!» አለው:: ተጠቃሚውም እልህ ውስጥ ገባና «አልወርድም!» አለ:: አሽከርካሪው ዳር አስይዞ ቀበቶውን ፈትና በሩን በርግዶ ወረደ:: የተጠቃሚዎች መውጫ በር ግን እንደተዘጋ ነው:: ተጠቃሚው ከቦታው ተነስቶ ወደ በሩ ሲንደረደር ከፊት ያሉ ሰዎች ያዙት:: መስኮት ከፍቶ አሽከርካሪውን «ወንድ ከሆንክ ክፈተው!» እያለ መሳደብ ጀመረ:: አሽከርካሪው ወደ ቦታው ተመልሶ በስሜት ረስቶት የነበረውን በር ከፈተና ሰውየው ካልወረደ እንደማይሄድ ተናገረ::

ከብዙ ትርምስ፣ ጭቅጭቅና ልመና በኋላ ታርቀው ጉዞ ተጀመረ::

እነዚህን ሁለት ነጠላ ምሳሌዎች ያመጣሁት ለማሳያ እንጂ ሁሉንም ይወክላሉ ብዬ አይደለም:: እንዲህ አይነት ብዙ አጋጣሚዎች አሉ:: ግን ለማሳያ እና ለምሳሌ ይሆናሉ::

እስኪ ልብ በሉ! በመጀመሪያ ሰርቪሱ ውስጥ የገባው ተጠቃሚ ማስጠንቀቂያውን አያውቅም:: ግዴለም! የሰርቪስ ሕግና ደንብ ስለሆነ (ለበቆሎና ለቆሎ ልዩ ዝርዝር ባይኖረውም) ተጠቃሚ እስከሆነ ድረስ ክልክል መሆኑን ማወቅ ነበረበት እንበል:: በሁለተኛ ደረጃ ግን አልገዛም፤ «ተው!» ሲባል ትቶታል:: በዚያ ላይ ደጋግሞ ይቅርታ ጠይቋል:: ሰው እንዴት ይቅርታ በተጠየቀ ቁጥር እየባሰበት ይሄዳል?

ከአንዳንድ ሰዎች የተረዳሁት ነገር ከትሕትና፣ ከቅንነት እና ከይቅርታ ይልቅ ግልምጫ፣ ስድብ እና ቁጣ ይገዛቸዋል:: ለምሳሌ የታክሲ ረዳቶችን ልብ በሉ! ተጠቃሚዎች በቁጣ «ወራጅ አለ!» ሲሉ፤ ለምን በቁጣ ይናገራሉ እያልኩ እናደድ ነበር:: የሚገርመው ግን ረዳቶቹ ተሽቁጥቁጠው የሚያስተናግዱት የሚያመናጭቃቸውን ሰው ነው:: ስለትሕትና እና ቅንነት ታክሲውን ጥቅስ በጥቅስ ቢያደርጉትም በቅንነት የሚያናግራቸውን ሰው ግን ያመናጭቃሉ:: መልስ እንኳን በትሕትና ሲጠየቁ «ይሰጥሃላ! ልትሞት ነው እንዴ!» እያሉ ይናገራሉ:: በትሕትና «እዚህ ጋ ታወርደኝ» ሲባሉ «አደባባዩ ላይ አይሻልሽም?» እያሉ ያሾፋሉ:: እንዲህ አይነት ሰዎች ከትሕትና ይልቅ ግልምጫ ይገዛቸዋል ማለት ነው::

ትሕትና እና ቅንነት የመሠልጠን ምልክት ነው:: በተቃራኒው ስድብ እና ግልምጫ የኋላቀርነት እና የበታችነት ስሜት ምልክት ነው:: መሳደብን እንደ ድፍረት የሚያዩ ይኖሩ ይሆናል፤ ግን አይደለም፤ የተጠራጣሪነት እና በራስ ያለመተማመን ምልክት ነው:: በራሱ የሚተማመን ሰው ቅን እና ትሑት ነው::

ቅንነት ጤና ነው:: በቅንነት ስናስብ የሰውነታችንን ህዋሶች አንጎዳም:: ህሊናችንን አንረብሽም:: የጥፋተኝነት ስሜት አይፈጠርብንም:: በውስጣችን የፀፀት አሻራ አይቀመጥብንም:: እልህ ግን በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በሳይንስም የተወገዘ ነው:: ለጤና ጎጂ ነው:: የስነ ልቦና ባለሙያዎች እንደሚሉት በቀል እና እልህ ውስጥ ስንገባ የጭንቅላታችን ህዋሶች ይጎዳሉ::

ቅንነት ማኅበራዊ ሕይወትን ለማሳለጥ ብቻ ሳይሆን ለአካላዊና አዕምሯዊ ጤናም ነውና ቅን እንሁን!

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ ሁለት የኢራን ሳተላይቶችን ጨምሮ 53 ሳተላይቶችን አመጠቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ በመሬት ላይ ያለውን ከባቢያዊ የአየር ሁኔታ የሚቆጣጠሩ ሁለት ሳተላይቶቸን እና ከኢራን የመጡ ሁለት ሳይተላይቶችን ጨምሮ 53 ሳይተላይቶችን የተሸከመ ሶይዙ ሮኬት ማምጠቋን ሮስኮስሞስ ስፔስ ኤጀንሲ አስታውቋል።

ኤጀንሲው እንደገለጸው ከሩሲያ ቮስቶቺኒ ኮስሞድሮም የተነሳው ሶይዙ ሮኬት የመሬትን አዮኖስፌር ክፍል ለመከታተል የሚያስፈልጉ ሎኖስፌራ-ኤም ሳተላይቶችን ወደ ሕዋ አምጥቋል። እንደ አሜሪካው የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ ከሆነ የመሬት ከባቢ አየር ከሕዋ ጋር የሚገናኝበት አዮኖስፌር ከመሬት ገጽ በላይ ከ80 እስከ 644 ኪሎሜትር ርቀት ይሸፍናል።

የእያንዳንዱ ሎኖስፌራ-ኤም ክብደት 430 ኪሎግራም ሲሆን የሚሠራበት ምሕዋር ወይም ኦርቢት 820 ኪሎሜትር መሆኑን ሮይተርስ የሩሲያውን ኢንተርፋክስ ዜና አገልግሎት ጠቅሶ ዘግቧል። ሮስኮስሞስ እንደገለጸው ቀጣዮቹ ሁለት መሣሪያዎች እ.አ.አ. በ2025 ይላካሉ።

ከ53 አነስተኛ ሳተላይቶች ውስጥ የኢራኖቹ ከፍተኛ የምስል ጥራት ያለው ሳተላይት እና አነስተኛ የኮሙኒኬሽን ሳይተላይት እንዲሁም የመጀመሪያው የሩሲያ-ቻይና ተማሪዎች ሳተላይት ይገኙበታል ተብሏል።

ሩሲያ ባለፈው የካቲት ወር የኢራንን መልክዓ ምድር የሚያስስ ሳተላይት ወደ ሕዋ ማምጠቋን በወቅቱ ተዘግቦ እንደነበር አል-አይን ኒውስ ዘግቧል፡፡

## ዚምባቡዌ ፖሊሶች ለሥራ ሲሠማሩ ሞባይል ስልካቸውን እንዳይጠቀሙ አገደች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዚምባቡዌ መንግሥት ፖሊሶች ለሥራ ሲሠማሩ ሞባይል ስልክ እንዳይዙና እንዳይጠቀሙ አገደ።

ሁሉም ፖሊሶች ለሥራ ሲሠማሩ ስልካቸውን ለበላይ ኃላፊዎቻቸው አስረክበው መውጣት እንዳለባቸውም አሳስቧል።

ለፖሊሶች ተልኳል የተባለው የማሳሰቢያ መልዕክት መንስኤ እና ዓላማው ግን አልተጠቀሰም።

ከእረፍት ሰዓት ውጪ ፖሊሶች ሞባይል ስልካቸውን መጠቀም እንዳይችሉ የተላለፈው ውሳኔ ሙስናን ለመቀነስ ያለመ ሊሆን እንደሚችል ቢቢሲ ዘግቧል።

ሁለት የትራፊክ ፖሊሶች ከሰሞኑ አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻዎችን እና ሞተሮችን እያስቆሙ ከአሽከርካሪዎች ጉቦ ሲቀበሉ የሚያሳይ ምስል ተለቋል።

ቪዲዮው ወትሮውንም በሙስና የተዘፈቁ ናቸው የሚባልላቸውን የሀገሪቱን የትራፊክ ፖሊሶች ገመና የገለጠ ነው በሚል መነጋገሪያ ሆኖ ነበር።

የዚምባቡዌ ፖሊስ ቃል አቀባይ ፖል ንያቲ ሁለቱ ጉቦ ሲቀበሉ የታዩ የትራፊክ ፖሊሶች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተናግረዋል።


"ለፖሊስ አገልግሎት የማይመጥኑ" ሲሉ የገለጿቸውን ባልደረቦቻቸው አስተዳደራዊ ቅጣትና የወንጀል ክስ እንደሚጠብቃቸውም ነው የገለጹት።

ደቡብ አፍሪካዊቷ ሀገር ዚምባቡዌ ተቋማት በሙስና ቢፈተኑም የትራፊክ ፖሊሶች ያፈጠጠ ጉቦ የመጠየቅ ልምድ ግን አሳሳቢ ስለመሆኑ ዜናዎች ያነሳሉ።

ሐራሬ ባለፈው ወርም ይህንኑ ችግር ይቀንሳል ያለችውን ውሳኔ አሳልፋ ነበር፤ ፖሊሶች ለሥራ ከጣቢያ ሲወጡ ስልካቸውን እንዳይዙ የሚከለክል መመሪያ አውጥታ ተፈጻሚ ግን አልሆነም።

"ምንም እንኳን ተደጋጋሚ ማሳሰቢያ ብናሰማም ትዕዛዙን የበላይ አዛዦች ሊያስፈጽሙት አልቻሉም" የሚለው አዲሱ የእገዳ ደብዳቤ፥ ፖሊሶች ከምሳ ሰዓት እና ከእረፍት ውጪ ስልካቸውን በሥራ ሰዓት መጠቀም እንደማይችሉ አመላክቷል።

የተላለፈውን ውሳኔ የማያስፈጽሙ የፖሊስ አመራሮች ስልካቸውን ይዘው ለሥራ ወጥተው በተገኙት ፖሊሶች ምትክ ለግዳጅ እንዲሠማሩ ይደረጋሉም ነው የተባለው።



ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

# አረንጓዴ ኢኮኖሚ የምድር ፈውስ - የልማት መድህኒት

ታሪኩ ዘለቀ

በዓለማችን የኢንዱስትሪው አብዮት ከታወጀ ወዲህ የአየር ንብረት ባህርይ ተቀያይሯል፡፡ በሂደት ቀድሞ የነበረው ይዞታ እየተለወጠ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ በየግዜው ጎርፍ፣ የሰደድ እሳት፣ ከመጠን ያለፈ ሙቀት፣ ድርቅ እና የመሳሰሉት አስከፊ የተፈጥሮ አደጋዎች መከሰቱ የዓለማችን መገለጫ ሆኗል፡፡ ይህ አይነቱ ክስተት በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በእስያ፣ በአፍሪካና በሌሎች አህጉራት ላይ እያሳደረ ያለው ጫና፣ የፍጥረታት ሕይወት መጥፋትና የንብረት መውደም እለት ከእለት እያሳየ፣ እያሰማን ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የአየር ንብረት ለውጥ ዓለማችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ እንደዋዛ በቀላሉ የሚነገርለት ቃል አይደለም፡፡ በየግዜው በሕይወታችን ያለ ስጋትና እየጎዳን የሚገኝ መሆኑን ጭምር የዓለም ሕዝብ ተረድቶታል፡፡ ምናልባትም እያደረሰ ያለው ጉዳት በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ዓለማችን በሙቀት፣ በጎርፍ፣ በበሽታ፣ በድርቅ ምክንያት ከጦርነቶች ሁሉ በላቀ ደረጃ ልትጠቃና ልትወድም እንደምትችል ሳይንቲስቶች ይተነብያሉ፡፡

ሳይንቲስቶቹ ለዚህ ለዓለማችን የጉዳት ቁንጮ ለሆነው ችግር እንደሁነኛ መፍትሄ እየመከሩ ያሉት አረንጓዴ ኢኮኖሚን ከፍ ማድረግንና መገንባትን ነው፡፡ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ስድስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራትን ይጠይቃል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ፕሮግራም /ዩኤንኢፒ/ በየዓመቱ በሚያወጣቸው ሪፖርቶች መሰረት ከውሀ፣ ከንፋስ፣ ከፀሀይ፣ከእንፋሎትና ከመሳሰሉት ተፈጥሯዊ ነገሮች የሚገኝን ታዳሽ ኃይል መጠቀም፣ለአየር ንብረቱ ተስማሚና ሙቀት አማቂ ጋዞችን የሚቀንሱ አረንጓዴ ግንባታዎችን መገንባት፣ ወሳኝነት አለው፡፡ ለአየር ንብረት ተስማሚነት ቀጣይነት ያላቸውና አስተማማኝ የሆኑ እንደ የኤሌክትሪክ መኪና፣ ብስክሌትና የመሳሰሉትን መጓጓዣዎችን መጠቀም የግድ ይላል፡፡ እንዲህ መሆኑ የውሃ አጠቃቀምንና አጠባበቅን፣ የቆሻሻ አወጋገድን፣ የመሬት አጠቃቀምና አጠባበቅን በአግባቡ ለማስተዳደርና አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ያግዛል፡፡

እነዚህን መሰረታዊ ግብዓቶች የሚያሟሉ ሀገራት በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ውስጥ መኖራቸው እንደሚረጋገጥም መረጃው ይመሰክራል፡፡ እኤአ ከ2007 በኋላ ዓለማችን ላይ 1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ዶላር በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ላይ ኢንቨስት ተደርጓል፡፡ አሁን ደግሞ ይህ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱ በግልፅ ይታያል፡፡ በተለይ በፀሀይ፣ በንፋስ፣ በእንፋሎትና በውሃ ኃይል ላይ እየተደረገ ያለው ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን ልብ ይሏል፡፡

በዓለም ሙቀት መጨመር ምክንያት እየደረሰ ያለው ጉዳት በጉዳዩ ላይ አመኔታ ያልነበራቸው ሀገራት ጭምር ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትኩረት እንዲሰጡ እንዳደረጋቸው ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ 63 ከመቶ የአውሮፓ ሕብረት ነዋሪዎች፣ 59 በመቶ የሚሆኑ እንግሊዛውያን፣50 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን እና 60 ከመቶ የሚሆኑ ቻይናውያን በአረንጓዴ ኢኮኖሚው እናምናለን እያሉ ነው፡፡ እነዚህ ሀገራት ለዓለም ሙቀት መጨመር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ቢሆኑም ከዚህ ቀደም በአረንጓዴ ኢኮኖሚ የሚያምኑ አልነበሩም፡፡

በዓለም ሙቀት መጨመር ሳቢያ አህጉረ አፍሪካ ደግሞ ባልበላችው ዳዋ እየተመታች ትገኛለች፡፡ ብዙ ችግሮችም እየደረሱባት የምትገኝ አህጉር ናት፡፡ አፍሪካ አረንጓዴ ኢኮኖሚን የምትከተል ከሆነ ለወጣቶቿ የስራ እድልን ከመፍጠር ጀምሮ ብዙ ጥቅሞችን እንደምታገኝ ዕሙን ነው፡፡ በአፍሪካ እስካሁን በተተገበረ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ብቻ ሶስት ሚሊዮን ወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ እርግጥ ነው በአፍሪካ በየዓመቱ 12 ሚሊዮን ወጣቶች ስራ ፈላጊዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች በስራ ለመሰማራት ብቁ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ እኤአ እስከ 2030 አፍሪካ ውስጥ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ እስከ 1 ትሪሊዮን ዶላር የኢኮኖሚ መሰረት ሊሆን እንደሚችል ይተነበያል፡፡

በኦክስፎርድ ጥናት መሰረት ዓለማችን የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ በማድረግ ብቻ 3 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ዶላር ገቢ ታገኛለች፡፡ ይህ ቁጥር እኤአ በ2050 ደግሞ ወደ 10 ትሪሊዮን ዶላር እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡ በአመዛኙ ይህ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫ ከሚያደርጋቸው ነጥቦች መካከል ምቹ የስራ ሁኔታን ለዜጎች ከመፍጠር አልፎ ስራ አጥነትን እስከ መቀነስ ብሎም የተረጋጋ ሀገራዊ ምርትን እስከማስቀጠል ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡፡

> **በኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ የተተከሉ ችግኞች የአርሶ አደሩን ማሳ ምርታማነት በማሳደግም ጉልህ ድርሻ አላቸው**

በአሁኑ ሰዓት በዓለማችን ከ73 ሚሊዮን በላይ ስራ የሌላቸው ወይም ስራ እየፈለጉ ያሉ ወጣቶች እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህንን የዓለማችን ችግር ለመፍታት የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተግባራዊነቱም በትሪሊዮን የሚቆጠር ዶላር ገቢ ከመገኘቱ ባሻገር ግብርናን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሚኖረው አዎንታዊ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ሀገራት ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትኩረት የሚሰጡ ከሆነ ለወጣቶቻቸው ትልቅ የስራ እድል ይፈጥራሉ፤ኢኮኖሚያቸውንም ያነቃቃሉ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያም ከዓመታት በፊት በጀመረችው አረንጓዴ አሻራን የማኖር ተግባር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የመገንባት አቅም ታላቅና ሰፊ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡ የዘርፉ ምሁራንም በምግብ ራስን ከመቻል እስከ ግዙፍ ኢኮኖሚ ግንባታ ድረስ ሚና ያለውን ተግባር እንደሀገር አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን ያሳስባሉ፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር እንደባህል ፀንቶ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም፣ የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣የድርቅ፣የጎርፍና የረሀብ አዙሪትን ጥሶ ለመውጣት የታቀደ መርሀ ግብር ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ከ2011 እስከ 2014 ወደ 25 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የመጀመሪያው ዓመት በ2015 ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በድምሩ በሀገራችን በነዚህ ዓመታት ከ32 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ ባለፈው ዓመት በ2016 ዓ.ም ደግሞ 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ከእቅዱ በላይ ተፈፅሟል፡፡

የባለፉት ዓመታት ክንውኖች ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ፋይዳዎችን በወጉ መረዳቷን ያመላክታሉ፡፡ ሂደቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ መርሀ ግብር መሆኑና ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ ምርቶችን እንደሚሰጥ ታምኖበትም እየተሰራበት ይገኛል፡፡ እስካሁን ከተተከሉት ችግኞች መካከል 60 በመቶ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው እነ ማንጎ፣ፓፓያ፣አቡካዶና የመሳሰሉት ፍራፍሬዎች ናቸው፡፡ የእንስሳትን የወተት ምርት ለማሳደግ፣ ለመኖና ለንብ ማንቢያ ምቹ የሆኑ የዕፀዋት ዝርያዎች ተተክለዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ተጨማሪ ምርቶችን በማስገኘት ስርዓተ ምግብንም በማሻሻል የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም፡፡

በኢትዮጵያ በተተገበሩ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሮች እንደ ሀገር የተቀመጡ የልማት ግቦች እንዲሳኩ መሰረት ተጥሏል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ተግባራት ከፍተኛ ተጠቃሚ የሚሆነው የግብርናው ዘርፍ ነው፡፡ እይታችን የሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ሲሆን ደግሞ ‹‹አረንጓዴ አሻራ›› በሚለው አካሄድ ሁለንተናዊ የሆነውን ሀገራዊ አቅም ማሳደግ ላይ የሚኖረው ጥቅም ከፍ ይላል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ ጉዞ የተመጣጠነ ዝናብን ከመስጠት ጀምሮ ለምነትን ለመመለስ ጥቅሙ ግዙፍ የሚባል ነው፡፡ በኢኮኖሚው ላይም ትልቅ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያሳርፋል፡፡ የተስተካከለ ዝናብ ሲኖር አፈር እንዳይሸረሸር ይከላከላል፣ የሰው ንብረት እንዳይወድም ስለሚያደርግ ምርታማነት ይጨምራል፡፡ ምርታማነት በጨመረ ቁጥር የሀገር ኢኮኖሚ እያደገ ይሄዳል፡፡ ለውጡ ወዲያው የሚታይ ላይሆን ቢችልም ቆይቶ ተጨባጭ የሚባሉ ለውጦች መመዝገባቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡

በ2016 ዓ.ም በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በአንድ ቀን ብቻ 615 ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል፡፡ ይህ እውነት ስንተባበር ምን ማድረግ እንደምንችል አንዱ ማሳያ ነው፡፡ እነዚህን ችግኞች መትከላችን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ሆነ ለመላው ዓለም ትልቅ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው፡፡ እኛ ዘመናችን ላይ ቆመን አያት ቅድመ አያቶቻችን እንደምናመሰግነው ሁሉ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችንም ነገ ከነገወዲያ ያመሰግኑናል፡፡ በእኛ ግዜ ካወደምነው የደን ሽፋን 3 በመቶ ያህሉን ሸፍነናል፡፡ እንዲህ ይባል እንጂ ቀደምቶቻችን ደግሞ ተገቢውን ግዴታ ከውነው አልፈዋል፡፡

በቀደመው ጊዜ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን 40 በመቶ ይደርስ እንደነበር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በ 1980ዎቹ በተደረገ ጥናት የደን ሽፋኑ አዘቅዝቆ 3 በመቶ መድረሱን አመላክቷል፡፡ ይህንን አስጊ ሁኔታ ለመቀየር ባለፉት ዓመታት በተሰሩ ስራዎች የደን ሽፋኑ 23 ነጥብ 6 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ የኢትዮጵያ ዓላማ የደን ሽፋኑን ቢያንስ 40 በመቶ ማድረስ ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ሰፊ የቆዳ ስፋት ያለው ሀገር የደን ሽፋኑ 3 በመቶ ብቻ መሆኑ እጅግ አስጊ ነው፡፡ በሀገራችን ምዕራብ በኩል የሰሀራ በረሀ ስጋት ‹‹መጣሁ መጣሁ›› እያለ ከሱዳን ጥግ ደርሷል፡፡ በምስራቅ በኩልም የሱማሊያ መልከአ ምድር አሸዋማ፣ በረሀማ ቦታ ነው፡፡ በስተሰሜንም የአረብ በረሀን እናገኛለን፡፡ በበረሀዎች የተከበበች ሀገር 3 በመቶ ብቻ የደን ሽፋን ካላት ምንያህል እንደምትጎዳ ግልፅ በመሆኑ ስጋቱን ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡

አሁን ላይ ግን ይህን ታሪክ እየለወጥነው እንገኛለን፡፡ ነገ ከነገወዲያ ደግሞ በደን ልማታችን የምንታወቅና ከደን ሀብታችንም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የምናፍስ ይሆናል፡፡

በተደጋጋሚ እንደሚሰማው ብራዚል ከደን ልማቷ ‹‹ሬድ ብላስ›› ከሚባለው ፕሮጀክት በየዓመቱ ከ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በላይ ስታገኝ ቆይታለች፡፡ ትልልቅ የሚባሉ የአውሮፓ ሀያላን ሀገራትም ለብራዚል ደኖች የሚከፍሉት ክፍያ አለ፡፡ ይህ ማለት ብራዚል ለአየር ንብረቷ መስተካከል ከደኗ ከምታገኘው ጥቅም ባሻገር ደን ስላላት ብቻ የምታገኘው ጥቅም አላት ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያም እየሄደችበት ባለው መንገድ የምትቀጥል ከሆነ እንደብራዚል ከሌሎች ሀገራት ክፍያ ማግኘቷ የማይቀር ነው፡፡ የሜትሪዮሎጂ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት ኮንጎ ያለው ደን ወይም ዛፍ ኢትዮጵያ ላይ ለሚጥለው ዝናብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው፡፡ልክ እንደ ኮንጎ ሁሉ ኢትዮጵያ ላይ የሚገኝ ደን የሰሜን አፍሪካ፣የምዕራብና የምስራቅ አፍሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የአውሮፓ ሀገራት ድረስ ይተርፋል፡፡ ሀገራችን ይህን አስተዋፅኦው በማበርከት የምታገኘው ገቢ ከመኖሩ በላይ ተግባሩ ኢትዮጵያን ሊያስመሰግን የሚገባ ነው፡፡

ይህ የደን ልማት ተግባር ዓለማችንን አንድ ትሪሊዮን ዛፎችን እንስጣት /እናልብሳት ‹‹ዋን ትሪሊዮን ትሪ ኢንሼቲቭ›› የሚባል ተነሳሽነትን ፈጥሯል፡፡ የተለያዩ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት በዓለማችን እስከ 3 ትሪሊዮን የሚደርሱ ዛፎች አሉ፡፡ በእርግጥ እነዚህ ዛፎች በአብዛኛው ሰፋፊና ትልልቅ በሚባሉና ወደ ሰሜን ዋልታ የሚጠጉ ሀገራት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ዛፎቹ እንደሩሲያ፣ ካናዳ፣ ቻይና፣ አሜሪካና የመሳሰሉት ሀገራት የሚገኙ ናቸው፡፡

በደቡብ ዋልታ ግዙፍ ደን ያላቸው ሀገራት እምብዛም አይገኙም፡፡ ከምድር ወገብ ወደ ላይ ስንወጣ የአማዞንና የኮንጎ ጥቅጥቅ ደኖች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ወደታች እየወረድን ስንሄድ የምናገኘው ደን አይኖርም፡፡ ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያ እየከወነች ያለችው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ደን እንዲኖር የምታደርገው አንዱ ጥረት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ የተተከሉ ችግኞች የአርሶ አደሩን ማሳ ምርታማነት በማሳደግም ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡ የአፈሩ መከላትና በጎርፍ መሸርሸር የግብርናው ዘርፍ ትልቁ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ ምንም ልባስ የሌለው ማሳ ላይ ዝናብ ሲጥል አፈሩ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚሸረሸር ይህንን ለመከላከል የተተከሉ ችግኞችም አሉ፡፡ እነዚህ ችግኞች የአፈር ለምነት የማስጠበቅ፣ የማሳደግ፣ አፈሩ በጎርፍ እንዳይሸረሸር በማድረግ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ያሳድጋሉ፡፡

ለምሳሌ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ሲጀመር የበቆሎ ምርት በሔክታር 25 ኩንታል ይመረት ነበር፡፡ አሁን ላይ በሔክታር 42 ኩንታል ደርሷል፡፡ በእርግጥ ይሄንን አረንጓዴ አሻራ ብቻ ያመጣው አይደለም፡፡ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያና የተሻለ አስተራረስ መጠቀም ጭምር አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የአፈር ለምነት መጨመሩ የአየር ሚዛኑን በመጠበቅ ምርታማነትን ለማሳደግ ተችሏል፡፡ በስንዴ ምርትም ከ19 እና 20 ኩንታል አሁን ላይ በሔክታር ወደ 36 ኩንታል ሊያድግ ችሏል፡፡

በስራ እድል ፈጠራውም አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ባለፉት ሶስት ዓመታት የአረንጓዴ አሻራ ያስገኘውን የስራ እድልና ተያያዥ ጉዳዮች በተመለከተ ባደረገው ጥናት ወጣቶች ተደራጅተው ችግኞችን በማፍላት፣ በመንከባከብ ስራ ላይ በመሰማራታቸው 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ተገኝቷል፡፡ 800 ሺህ የሚጠጋ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ይህ የሚያሳየው በመርሀ ግብሩ መተግበር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍ ማለቱን ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል፣ የደን ሽፋንን በመጨመር፣ የተፈጥሮ ብዝሀ ሕይወት ሚዛንን ለማስጠበቅ በሚደረግ ጥረት የደን ሽፋንን መጨመር ዋንኛው የመርሀ ግብሩ ተልዕኮ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ የሚመጣው አማቂ ጋዞችን በአካላቸው የሚይዙ እፀዋት ባለመኖራቸው፣ የተራቆቱ ተራሮችና አካባቢዎች በመፈጠራቸውና የሚዘንብ ዝናብ በምድር ላይ ጎርፍ ሆኖ በመሄዱ ምክንያት ነው፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የኢትዮጵያን ደን ሽፋን ከዓመታት በኋላ ከፍ እንዲል አስችሏል፡፡ ከዚህም ባሻገር በርካታ ለምግብነት የሚውሉ ዛፎች በመተከላቸው ምክንያት ዜጎች ለምግብነት አገልግሎት የሚውሉ እፅዋቶችን በቀላሉ እንዲያገኙና ሸጠውም የገቢ ምንጭ እንዲሆናቸው አስችሏል፡፡

እናም በሚደረገው የአረጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሀገራችን የወጠነችው የልማት ግብ ማሳኪያ መንገድ መሆኑን ተረድተን ለስኬቱ ይበልጥ በጋራ መቆም ይጠበቅብናል፡፡ ሀገርን በማልማት ፈጣን ጉዞ ለየቅል ዕሳቤ መኖር የለበትም፡፡ በ2030 እንደርስበታለን ተብሎ የተቀመጠው የ30 በመቶ ሀገራዊ የደን ሽፋን በአግባቡ ይሳካ ዘንድ ዜጎች በልማቱ ላይ በሚደረገው ያላሰለሰ ርብርብ ከፍተኛ ተሳትፎና ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ እውነታ በተግባር በተመሰከረ ቁጥር የምንፈልገውን ሀገራዊ እድገት ማስመዝገብ ይቻለናልና፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# የትዝታው ንጉሥ

ክብረአብ በላቸው

የኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ ጉዞ መነሻ እየተደረገ በታሪክ የሚነሳው የ40ዎቹ የአርመን ልጆች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት እና የማርሽ ባንድ ማቋቋም ነው። ይሁን እንጂ ገና በአጼ ምንሊክ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሙዚቃ ቡድን የማቋቋም ሙከራዎች ነበሩ።

ፍራንሲስ ፋልሴቶ ስለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ጉዞ በጻፈው ማስታወሻ ይህን ሃሳብ አስፍሯል፤ አጼ ምንሊክ አድዋ ላይ ጣሊያንን ድል ካደረጉ በኋላ የሩሲያ ሳር (tsar) ንጉሱን እጅ ለመንሳት አምባሳደራቸውን ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። አምባሳደሩ ለንጉሱ ይዞ ከመጣው እጅ መንሻ መካከል 40 የብራስ የሙዚቃ መሳሪያዎች ይገኙበት ነበር።

የሙዚቃ መሳሪያ የአጨዋወት ሞያ ለማሰልጠን ደግሞ ሚሌውስኪ (Milewski) የተባለ የሙዚቃ መምህር አብሮ ተልኮ ነበር። ሚሌውስኪም ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ሙዚቃ ለማስተማር ጥረት ያደርግ ነበር። ከዚህ ከፋልሴቶ ማስታወሻ እንደምንረዳው፤ የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ የዘመናዊ ሙዚቃ ጉዞ በር ከፋች ጭምር ነበር።

ከላይ የተጠቀሱት የታሪክ አጋጣሚዎች እንዳሉ ሆነው በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ እጅጉን ያበበበት እና ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሰበት ዘመን ከ1947 ዓ.ም. እስከ አብዮት ፍንዳታ ድረስ ያሉት ሀያ ዓመታት ናቸው። እኚህ 20 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ወርቃማ ዓመታት ነበሩ። ቀደም ብለው ተቋቁመው የነበሩት የተለያዩ ወታደራዊ ባንዶች ምርጥ ምርጥ ድምጻውያንን በመመልመል አዳዲስ ሙዚቃዎችን እያጠኑ ብቅ ማለት ሲጀምሩ የአጼ ኃ/ሥላሴ እና የሀገር ፍቅር ትያትር ቤቶችም መድረኩን በመቀላቀል ምርጥ ምርጥ ሙዚቃዎችን እያዘጋጁ ማቅረብ ጀመሩ።

በ1950ዎቹ መጨረሻ እና በ1960ዎቹ እንደ ራስ ባን ያሉ የግል ባንዶች በብዛት መቋቋም ጀመሩ። ይህ ጊዜ የተለያዩ እውቅ ሙዚቀኞች ወደ መድረክ የመጡበት እና የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ ከምዕራቡ ዓለም ሙዚቃ ጋር እየተዋሃደ የራሱን ቀለም እና መስመር መያዝ የጀመረበት ጊዜ ነበር።

በዚያ ዘመን ከመጡና በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ የማይነጥፍ አሻራቸውን ማኖር ከቻሉ ስመ ጥሩ አቀንቃኞች መካከል አንዱ ማሕሙድ አሕመድ ነው:: በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅነትን፣ ተደናቂነትን፣ ተፈቃሪነትን ማትረፍ የቻለ ፈርጥ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ:: ሙሉ ሕይወቱን በሙዚቃ ያሳለፈው ማሕሙድ በሙዚቃው ይተነፍሳል፣ ይናገራል፣ ሰውን ያዝናናል ይባልለታል።

ከ60 ዓመታት በላይ በቆየውም የሙዚቃ ሕይወቱ የተለያዩ ትውልድን በሙዚቃው አንድ ላይ ማምጣት የቻለ ትልቅ አርቲስት ነው:: በተለያዩ ኮንሠርቶች በሚዘፍንበት ወቅት በተለያዩ የዕድሜ ክልሎች የሚገኙ ሰዎች ብሔራዊ መዝሙር በሚመስል መልኩ አብረውት በመዝፈንም በዘፈኑ አንድነትን ያሳያሉ::

ማሕሙድ የዝና ጣራ ላይ መድረስ ችሏል:: በሕዝቡ ዘንድ ከመወደዱ በተጨማሪ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይም ዝናው ናኝቷል:: የሰዎችን ልብ ከማሸነፉ በተጨማሪ ከኮንሠርቱ በፊት ቲኬቶቹ ተሸጦ የሚያልቅበት አጋጣሚም ተደጋጋሚ ነው:: የተለያዩ ሽልማቶችንም ለማሸነፍም ችሏል:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የቢቢሲ ወርልድ ሚዩዚክ አዋርድ አንዱና ዋነኛው ነው:: ምንም እንኳን ይሔን ያህል የጣራ ዝና ላይ ቢሆንም ትሁት፣ ሰዎችን የሚያከብርና በቀላሉም የሚግባባ ሰው እንደሆነ ይነገርለታል።

በ1933 ዓ.ም. በሰባት ቤት ጉራጌ ቦዠበር የተወለደው ማሕሙድ፤ ዕድገቱ ደግሞ በአዲስ አበባ አሜሪካን ግቢ አካባቢ ነው:: ሥራንም ሆነ ሕይወትን በራሱ መጋፈጥ የጀመረው ገና በሕፃንነቱ ነበር:: አባቱ በሚሠራበት ግሪክ ክለብ አብሮ በመሔድ ቅርጫት ኳስና የቴኒስ ሜዳዎቹ ላይ ይሠራም ነበር:: በስድስት ዓመቱም ሊስትሮ ሆኖ መሥራት እንደጀመረም ይነገራል::

በትምህርት ቤት ቆይታው ብዙ ጉበዝ እንዳልነበር ፈገግ ብሎ የሚያወራው ማሕሙድ፤ ቤተሰቦቹንና ራሱን መርዳት እንዳለበትም የተረዳው ገና በሕፃንነቱ ነበር:: የሙዚቃ ሕይወቱ ሀ ብሎ የተጀመረው ደግሞ፤ አንድ ክለብ ውስጥ ሳንድዊች እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ጊዜ ነው:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዚያው ክለብ ውስጥ ጥላሁን ገሠሠ ይዘፍንበት ነበር::

በአንድ አጋጣሚም ሁሉም ድምፃውያን ወደ ድሬዳዋ ሔደው ሙዚቀኞቹ ያለ ድምፃዊ እየተለማመዱ ነበር:: የተፈራ ካሣን «አልጠላሽም ከቶ»ን የተዘራን «ይሔም አለ ለካ»ንና የጥላሁን ዘፈን እየተለማመዱ ነበር:: በድምፅ መዝፈን እንደሚፈልግም ጠየቃቸው::

«በጣም ቀጭን ነበርኩ እናም 'ትችያለሽ? ወይ» ብለው ጠየቁኝ፣ እኔም እሞክራለሁ አልኩ» በማለት ማሕሙድ ይናገራል:: «አልጠላሽም ከቶ» የሚለውን ዘፈን በሚዘፍንበት ሰዓት የኮንጐ ዘማቾች በቦታው ነበሩ፤ እናም አስደነቃቸው:: እንደገናም እንዲዘፍን ተጠየቀ:: የክለቡ ባለቤት በቦታው የነበረ ሲሆን፤ አድናቆት በተሞላ ድምፅም «የአላህ ያለ መዝፈን ትችላለህ!» እንዳለው ማሕሙድ ያስታውሳል:: በዚህም አጋጣሚ ከአስተናጋጅነት ወደ ዘፋኝነት ተቀየረ:: የቤቱ ባለቤትም ሙሉ ልብስ ገዛለት::

ጥላሁንና ሌሎቹ ዘፋኞች በተመለሱበት ወቅት የእሱ መዝፈን በጣም አስገረማቸው፤ የግጥም ደብተር ሰጡት:: መዝፈን በጀመረበት ወቅት የተለያዩ ዘፋኞችን ሙዚቃ ይዘፍን ነበር:: በዚህም ክለብ «አላወቅሽልኝም» የሚለው የመጀመሪያው ዘፈኑ የሆነው ግጥም ተሰጠው::

ክቡር ዘበኛ መቀጠር ፍላጐቱ የነበረ ሲሆን፤ መጀመሪያ ግን ፖሊስ ኦርኬስትራና ምድር ጦር ለመቀጠር ጠየቀ:: በተለያዩ ምክንያቶችም እንደማይቀጥሩት ነገሩት:: መቶ አለቃ ግርማ ሐድጉም (በኋላ ሻለቃ) ክቡር ዘበኛ መቀጠር ይፈልግ እንደሆነ ጠየቁት፣ እሱም ተስማማ ከመቀጠሩ በፊት ግን በሕዝብ ፊት ዘፍኖ ማለፍ ነበረበት:: የዚያን ጊዜ የነበረውን እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር በጥልቅ ያስታውሳል፤ የታምራት ሞላን «ተስፋ አትቁረጪ» እንዲሁም «አላወቅሽልኝም»ን ሲዘፍን የተመልካቹ መልስ ለየት ያለ ነበር::

«የኤልቪስ ፕሪስሊን ዳንስም እየደነስኩ ነበር፣ እናም የተመልካቹ መልስ የማይታመን ነበር፤» በማለት ማሕሙድ ይገልጻል:: መቶ አለቃ ግርማም ወታደር ሆኖ እንዳይቀጠር መከሩት፣ የክቡር ዘበኛ ሰዎችም በወታደርነትና ሙዚቀኝነት 120 ብር እንክፈልህ ብለው ጠየቁት፤ እሱ ግን ባለመስማማቱም በሙዚቀኝነት ብቻ በ1955 ዓ.ም. አካባቢ ተቀጠረ:: ለአሥራ አንድ ዓመታት ያህልም በዚህ ቦታ ሠርቷል::

«ለእዚህ ያበቃኝ፣ የማውቀውን ነገር ሁሉ ያስተማረኝ ለእኔ ወንድሜ ጥላሁን ገሠሠ ነው:: ሌሎችም ሙዚቀኞች እንዲሁ በእኔ ላይ አሻራ ጥለዋል፤» ይላል ማሕሙድ::

በዚያን ወቅት ሙዚቀኞች አንድ ላይ ይሰባሰቡበት የነበሩ ብዙ አጋጣሚዎች ነበሩ:: ከእነዚህም ውስጥ ክቡር ዘበኛ ይሠራ በነበረበት ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ይደረግ የነበረው የሙዚቀኞች ውድድር አንዱ ነው::

የተለያዩ ባንዶች እንደ ምድር ጦር፣ ክብር ዘበኛና የፖሊስ ኦርኬስትራ ባንዶች ከድምፃውያኖቻቸው ጋር ይመጣሉ:: እያንዳንዱም ድምፃዊ አንድ ወይም ሁለት ዘፈን ይዘፍናል:: ይሄም ለሙዚቀኞች ጥሩ አጋጣሚ እንደነበር ይናገራል:: ከአሥራ አንድ ዓመታት ቆይታም በኋላ በተለያዩ ክለቦች መሥራት ጀመረ:: ለዚህም ምክንያቱ የነበረው ያገኘው የነበረው 60 ብር አምስት እህቶቹና ወንድሞቹ በአጠቃላይ ቤተሰቦቹን መደገፍ ስለማይችል ነበር::

በወቅቱ አባቱ ሥራ ያልነበራቸው ሲሆን፤ የምትሠራው እናቱ ብቻ ነበረች:: መጨረሻ ላይ ከክቡር ዘበኛ በለቀቀበት ወቅት ደምወዙ 250 ብር ደርሶ ነበር፤ ከዚያም ከአይቤክስ ባንድ ጋር ተጠቃልሎ ራስ ሆቴል ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ:: በሙዚቃ ሕይወቱ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶችን እንዳሳለፈ የሚናገረው ማሕሙድ፤ ዘመኑ ለሙዚቀኞችም ሆነ ለሙዚቃ ዕድገት የተመቻቸ እንደሆነ ይገልጻል:: እንደሚናገረው ከሆነ ይሄ ዕድገትም የተገኘውና እዚህ መድረስ የተቻለው በድሮ ሙዚቀኞች መስዋዕትነት ነው ይላል።

«እነዚህ ሙዚቀኞች አሻራቸውን ጥለው ማለፍ ችለዋል፤» የሚለው ማሕሙድ በዚያን ጊዜ የነበሩት ሙዚቀኞች ምንም እንኳን ችሎታው ቢኖራቸውም የሙዚቃ ትምህርት ቤት አልሄዱም:: የዚያን ጊዜውንም በማስታወስ ለሙዚቀኞች እንዴት ከባድ እንደነበር ይናገራል:: ሙያውም እንዴት ይናቅ እንደነበርም ያስታውሳል::

በ1963 ከአይቤክስ ባንድ ጋር ራስ ሆቴል በሚሠራበት ወቅት «ኩሉን ማን ኳለሽ»፣ «አምባሰል»፣ «ችቦ አይሞላም ወገቧ» እና «አልማዝ ምን ዕዳ ነው» የመሳሰሉ ዘፈኖችን ይዘፍን ነበር:: እነዚህ ዘፈኖች ከአንዳንድ ወገኖች ከፍተኛ ትችትም አጋጠመው:: የዱሮ ዘፈኖችን በአዲስ መልክ ትጫወታለህ ለማለት አንድ ጋዜጠኛ «ፍራሽ አዳሽ» ብሎ የጠራውን አጋጣሚም አሁንም አይረሳውም::

«አላዘንኩም:: የድሮ ዘፈኖችን አዲስ ሕይወት በመስጠት ዘፍኛለሁ:: ፍራሽም እንደ አዲስ ሲታደስ ይተኛበታል» ይላል:: ማሕሙድ ከዚህም በተጨማሪ «ዓባይ ማዶ»፣ «ደኑን ጥሰሽ» እና «የት ነበርሽ» የሚሉት ዘፈኖቹም የተለየ ርዕዮተ ዓለም ያስተላልፋሉ በሚልም ተወቅሶ ነበር::

የማሕሙድ ዓለም አቀፍ ዕውቅና የመጣው ፍራንሲስ ፋልሴቶ ኢትዮጲክስ የሚለውን የሙዚቃ ስብስብ ካወጣ በኋላ ሲሆን፤ ማሕሙድም ውለታውን የረሳ አይመስልም:: ፋልሴቶ ፈረንሣዊ ፕሮሞተር ሲሆን፤ የማሕሙድን «መላ መላ» የሚለውን ዘፈን ሬዲዮ ላይ ሰምቶ አብረን እንሥራ ብሎ ጠየቀው፤ ማሕሙድ መጀመሪያ ላይ ተጠራጥሮ እንደነበር ያስታውሳል:: እየተደራደሩ ባሉበት በ1960ዎቹ አካባቢ ማሕሙድ ወደ ፈረንሣይ አቅንቶ ሙላቱ አስታጥቄ ጋር አብሮ ዘፍኗል::

ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ክቡር ዘበኛን በሲቪልነት በመቀላቀል ወደሙዚቃ የገባው አንጋፋው የትዝታው ንጉስ መሀሙድ አሕመድ በአዘፋፈን ችሎታው እና በድምፁ ውበት ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካ፣ አውሮፓ እና አሜሪካ ሳይቀር ሰፊ ተቀባይነት እና ተወዳጅነትን ያተረፈ ነው።

አርቲስት ማሕሙድ ከ60 ዓመታት በላይ በተሻገረው የጥበብ አበርክቶው ሀገሩን እና ወገኑን በከፍተኛ ፍቅር በብዙ ያገለገለ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ከባህላዊ ሙዚቃዎች ጋር አዋህዶ በመዝፈን በአገራችን የሙዚቃ ንጉስ ነው እስከመባል የደረሰ ታላቅ የጥበብ ሰው ነው።

የትዝታው ንጉስ ጋሽ ማሕሙድ አሕመድ በኢትዮጵያ ከ50 ዓመታት በላይ ከልጅነቱ አንስቶ የኢትዮጵያንን ሙዚቃ በተለያዩ ቋንቋዎች በመዝፈን የአገራችንን ሙዚቃ ከአገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲደመጡ ያስቻለ ያበረከተው አስተዋጽኦ ለአሁኑ ትውልድ አርአያ የሆነ የሙዚቃ ንጉስ ነው።

እኛም ድምፃዊ ማሕሙድ ከ60 ዓመታት በላይ የተሻገረው የሙዚቃ ሕይወቱን በክብር ለመቋጨት በወዳጅ አድናቂዎች አማካኝነት ዝግጅት እየተደረገ ባለበት በዚህ ወቅት ለሕዝብና ለሀገራቸው መልካም ያደረጉና በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ አሻራ ማኖር የቻሉ ግለሰቦች ታሪክ አንስተን ለአበርክቷቸው ክብር በምንሰጥበት የባለውለታዎቻችን አምድ ስም ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ዕድገት ለዋለው ውለታ አመሰገንን። ሰላም!



አርቲስት ማሕሙድ አሕመድ

# ስፖርት





## የጤና ቡድኖች የእግር ኳስ ውድድርና የአቃቂ ስፖርት መነቃቃት

**ዓለማየሁ ግዛው**

በስፖርት እንቅስቃሴ በስፋት ከሚታወቁ ክፍለ ከተሞች አንዱ አቃቂ ቃሊቲ ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ ለስፖርት ያለው ቅርበትና ፍቅር ልዩ ነው። በርካታ ስፖርተኞችም ከስፍራው ወጥተው ሀገርን እስከ መወከል ደርሰዋል። እግር ኳስ በአካባቢው ማኅበረሰብ በተለይም በወጣቶች በስፋት ከሚዘወተሩ ስፖርቶች ግንባር ቀደም ነው።

በአካባቢው በርካታ የጤና ቡድኖችና የታዳጊ ፕሮጀክቶች እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። በዚህም ለአካባቢው ስፖርት እድገትና መነቃቃት አስተዋፅዖ እያደረጉ ይገኛሉ። ከነዚህ መካከል በእድሜ ደረጃዎች የሚካሄዱት ውድድሮች አካባቢው ቀድሞ የሚታወቅበትን ጠንካራ የእግር ኳስ መነቃቃት እየመለሰ እንደሚገኝ እያመላከተ ነው። ይህም በአቃቂ ቃሊቲ የጤና ስፖርት ማኅበራት እግር ኳስ ውድድር ላይ ሊንፀባረቅ ችሏል። ውድድሩ የታዳጊ ፕሮጀክቶች እግር ኳስን መደገፍ ዓላማ አድርጎ ዘንድሮ ለአራተኛ ዓመት ከሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ ቆይቶ በቅርቡ ተጠናቋል።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ለሁሉም ኮሚቴ አወዳዳሪነት የተካሄደው ይህ «ሰመር ካፕ» የተሰኘ የጤና ስፖርት ማኅበራት ውድድር በሁለት የእድሜ እርከኖች 28 የጤና ቡድኖችን አሳትፏል።

እድሜያቸው ከ30 ዓመት በላይ የሆኑ 20 ቡድኖችና እድሜያቸው ከ40 ዓመት በላይ የሆኑ 8 ቡድኖች በውድድሩ ተሳታፊ ሆነዋል። እነዚህ ቡድኖች በአምስት ወራቱ የዙር ውድድር በሰበሰቡት ነጥብ መሠረት አሸናፊው ታውቋል። ከ30 ዓመት በላይ ውድድር የፍጻሜ ጨዋታ አቃቂ ወንድማማቾች ጤና




**አቃቂ ወንድማማቾች ጤና ስፖርት ማኅበር፣**

ስፖርት ማኅበር ከሞኩና ጓደኞቹ ቡድንን በፍፃሜ 4 ለ 2 በሆነ መለያ ምት አሸንፎ ፉክክሩ ፍጻሜ አግኝቷል። ከ40 ዓመት በላይ ውድድሩ ደግሞ ሞኩና ጓደኞቹ ጤና ስፖርት ማኅበር የዋንጫና የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆኗል። አቃቂ ወንድማማቾች ደግሞ ሁለተኛ እንዲሁም ሲዳ አዋሽ ወንድማማቾች ሦስተኛ በመሆን የሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል።

የክፍለ ከተማው የስፖርት ለሁሉም ማኅበር ሰብሳቢ አቶ ገዛኸኝ ምንድዬ፣ የአቃቂ ቃሊቲ ሰመር ካፕ የጤና ስፖርት ማኅበራቱ ከውድድር ባሻገር በሥራቸው የተተኪና ታዳጊ ወጣት ስፖርተኞች ፕሮጀክት በማቋቋም ድጋፍ እያደረጉና እያሠለጠኑ መሆኑን ተናግረዋል። ስፖርት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይም የስፖርት ማዘውተሪያን ከማስተካከል ጀምሮ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲደረግም ጥሪ አቅርበዋል።

የአቃቂ ቃሊቲ ስፖርት ማኅበራት ማደራጀት፣ እውቅናና ድጋፍ ባለሙያ አቶ ተካበ መካሻ፣ የውድድሩ ዓላማ ታዳጊ ወጣቶችን መደገፍ እንደሆነ ጠቅሰው፣ 28ቱም የጤና ስፖርት ማኅበራት የታዳጊ እግር ኳስ ፕሮጀክቶችን በሥራቸው እንደያዙ አስረድተዋል። በዚህም መሠረት ከፍተኛ ወጪ በማድረግ የመጫወቻ ኳስ ግዢ ተፈጽሞ ለሁሉም ቡድኖች ድጋፍ መደረጉን ገልፀዋል። ውድድሩ በስፖርት ለሁሉም ኮሚቴ አማካኝነት የሚካሄድ ሲሆን፣ ዘንድሮ የተሳታፊ ቁጥር መጨመሩንና የአካባቢው ኅብረተሰብም ማነቃቃቱን አክለዋል። ከመንግሥትና ኅብረተሰቡ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር እንዲሁም ትልልቅ ተቋማት ኮሚቴውን መደገፋቸውን አስታውሰውም፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ ውድድሩ ዓመቱን ሙሉ እንዲካሄድ ፍላጎት ማሳየቱን ጠቅሰዋል። አቃቂ ላይ ከአርባ በላይ የጤና ስፖርት ማኅበራት የሚገኙ በመሆኑ በቀጣይ እነሱን ያሳተፈ ትልቅ ውድድር ለማካሄድ መታቀዱንም አብራርተዋል። በከተማው ያለውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በትብብር ለማሠራት ቃል የገቡ ባለሃብቶች መኖራቸውም ተጠቅሷል።

የክፍለ ከተማው አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አለማየሁ ሚጀና፣ ውድድሩን ላዘጋጁ የስፖርት ማኅበራትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበው፣ ከተማዋን ምቹ ለማድረግ ከሚያከናወኑት ትልልቅ ፕሮጀክቶች ጎን ለጎን በአካልና በአዕምሮ የዳበረ ጤናማና አምራች ማኅበረሰብ ለመፍጠር በስፖርት ዘርፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንና በቀጣይም ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ በበኩላቸው፣ በተመለከቱት ነገር መደሰታቸውን ገልጸው፤ የጤና ስፖርት ማኅበራቱ ጤንነታቸውን ለመጠበቅ ውድድር ከማካሄድ በላይ ታዳጊዎችን አቅፈው መያዛቸውን አድንቀዋል። ተተኪና ወጣት ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚደረገ ጥረት የሚበረታታና ለማስቀጠልም ፌዴሬሽኑ ባለው አቅም ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልፀዋል። በውድድሩ ቡድኖቹ የማይመች ሜዳ ላይ እንደተጫወቱና፣ ይህንን ክፍለ ከተማውና የከተማ አስተዳደሩ ትኩረት እንዲሰጡበትም አመላክተዋል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አቃቂ ለሚገኙ የጤና ቡድኖች ሙያዊና የመጫወቻ ኳሶችን ድጋፍ እንደሚያደርግም ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን በበኩላቸው፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ከተማውን እና ሌሎች ደጋፊ አካላትን በማስተባበር ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንደሚሠራ ገልጸዋል።


## የሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ

የሰንዳፋ በኬ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት የማያገለግሉ ኬብሎች፣ የማያገለግሉ የመኪና ጎማዎች እና የማያገለግሉ ብረታ ብረቶችን አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጨረታው መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

1. የመስሪያ ቤት አድራሻ፡- ሰንዳፋ በኬ ከተማ አስተዳደር ዳሽን ባንክ ፊት ለፊት በሰንዳፋ በኬ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት በመቅረብ የማይመለስ ብር 500.00/አምስት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል የጨረታ ሠነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
2. የጨረታ ሰነዱን መግዛት የሚቻለው ዘወትር በሥራ ቀናት ከጠዋቱ 2:30-6:30 እና ከሰዓት በኋላ ከ7:30-11፡00 ሰዓት ብቻ ነው።
3. የንብረቶቹን ሁኔታ እስከ ህዳር 12/2017 ዓ.ም ዘወትር በሥራ ቀናት ከጠዋቱ 2:30-6:30 ሰዓት እና ከሰዓት በኋላ ከ7፡30-11፡00 ሰዓት ድረስ በጨረታ ሠነዱ ላይ በተገለጸው ቦታ በመገኘት ማየት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የሚያቀርቡትን ዋጋ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ህዳር 13/2017 ዓ.ም በሰንዳፋ በኬ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ቢሮ ቁጥር 4 ለጨረታው በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ህዳር 13/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ በ4:30 ተዘግቶ በዕለቱ በ4፡45 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
6. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ጨረታ መነሻ ዋጋ 1% የጨረታ ማስከበሪያ C.P.O በማዘጋጀትና ዋጋ ማቅረቢያው ኤንቨሎፕ ውስጥ በመክተት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የሰንዳፋ በኬ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት**

## INVITATION FOR BID
## IFB Reference No. ECWCT/NCB/PG/37/2017

The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) hereby invites registered eligible bidders for Supply & Install, Test and Commission Of Mechanical Work for Construction of 4B+M+G+21 Federal Document Authentication and Registration Agency Office Building Project) Under National Competitive Bidding -NCB).

1. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the Fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate, Online Supplier list Registration Certificate.
2. Bidding document should be prepared in English language.
3. Interested Potential Bidders can obtain a complete set of bidding document from the office of Procurement department against payment of none refundable fee of Birr 400.00 upon Presentation of Trade License renewed for the fiscal year; VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate and Online Supplier list Registration Certificate.
4. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision Indicated in bidding document.
5. The deadline for bid Submission shall be on November 28, 2024 at 03:00 PM.
6. Bid must be accompanied with a Bid Security of Than Birr 300,000.00 (Three Hundred Thousand) in the form of certified cheque (CPO) or Bank guarantee.
7. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department, before the closing date and time.
8. Bids will be opened on November 28 ,2024 at 03:30 PM, in Ethiopian Construction Works Corporation Procurement Department office, in the presence of bidders and/or their Representatives who choose to attend.

9.The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.

10. Bidders may get further information at the following address:

**Ethiopian Construction Works Corporation**
**Building Material Procurement Team**
**P. O. Box 21952/1000, Addis Ababa, Ethiopia**
**Gurd Sholla, In front of Andinet International School**
**Telephone No. 251-11- 8- 96 29 91/011 8 67 80 89/251-11-8 72 30 86**
**Telegram channel ## ECWC**

**Ethiopian Construction Works Corporation**

### ማስታወቂያ

በከሳሽ/ይግ/ባይ፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓ/ሕግ እና
በተከሳሽ/መ/ሰጪ፡- አቶ ሰለሙን ጌታቸው በሪሁ
መካከል ስላለው የወንጀል ክርክር የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት በ28/01/2017 ዓ/ም በሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ በ28/02/2017 ዓ/ም ከጧቱ 3:00 ሰዓት መቀለ ከተማ በሚሰየመው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ቀርበው እንዲከራከሩ ጥሪ እያስተላለፍን፤ ካልቀረቡ ግን መዝገቡ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍርድ ቤት አዟል።

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት**